የሐረር መስፍን
ልጆችን መኰንንን
በችግራችሁ ሁሉ
እንዲረዳችሁና
እንዲጠብቃችሁ
አድርገናል ።

ቀ፡ ኃ፡ ሥ፡

ከመጀመሪያዎቹ
የጦር ቦይስካውቶች
በሕብረት የተዘጋጀ
አጭር ታሪክ ።



በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ

4383
10.00
6.7.99

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ።

ግርማዊት እቴጌ ።

ልዑላትና ልዑላን ንጉሣዊ ቤተ ሰብ ።

ተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ ባጭሩ ሕይወታዊ ዘመናቸው የሠሩት ልዩ ልዩ የትሩፋት ሥራ እጅግ የበዛ ስለሆነ ለመልካም ሰውነት ምስክር ሆነዋል ።

ሞት ለሰው ልጅ ግዴታ ዕዳው በመሆኑ ወጣቱ መስፍን ቀድመው በሞት ስለተለዩ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ልቡ በኀዘን ጦር ተወግቷል ። ዳሩ ግን ወጣቱ መስፍን ከአብራካቸው የተከፈሉ ልዑላን ልጆቻቸውን አፍርተውልን ስላለፉ ፤ ይህን ብቻ በመመልከት ከኀዘን መጽናናት ይኖርብናል ።

ለሀገርና ለወገን የሚጠቅም ተስፋ የተጣለበት ታላቅ ሰው በሞት ሲለይ ጉዳቱ ለወላጆቹና ለቤተሰቦቹ ብቻ ሳይሆን ላገሩና ለወገኑ ጭምር ስለሆነ ኀዘኑም በዚሁ መጠን የመረረ ነው ። ዳሩ ግን ሁላችንም በተራ ወደምንጠራበት ዓለም ቀድመውን ቢሄዱም ትተውልን የሄዱቸውን ከከላቸው የተከፈሉትን ልዑላን ፍሬዎቻቸውን ስንመለከት ፤ በመካከላችን በሕይወት እንዳሉ አድርገን እናስታውሳቸዋለን ።

የመጀመሪያዎቹ የኢትዮጵያ የጦር በይስካውት ተማሪዎች በልዑልነታቸው የበላይ ጠባቂነትና መሪነት እንተዳደር በነበረ ጊዜ ፤ ልዑልነታቸው በትምህርት ቤቱና በተማሪዎቹ መካከል የፈጸሟቸውን ልዩ ልዩ ሥራዎችና የልዑልነታቸውም ሰብአዊ ርኅራኄ ተማሪዎቹን በፍቅር አገብሯቸው የፈጸሙትን አገልግሎት ባጭር የምታሳይ መጽሐፍ በሕብረት ስላዘጋጀን ለኀዘን መጽናኛና የልዑልነታቸው የሕይወት ሥራ መታሰቢያ እንድትሆንልን በታላቅ ትሕትና አበርክተናል ።

ፍጹም አገልጋይዎች የመጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውቶች ።

ነሐሴ ፳፮ ቀን ፵፱ ዓ ም

## መግለጫ ።

የስካውት ትምህርትን የመሠረቱ ፤ ሎርድ ሮበርት እስቲፋንሰን እስሚት ባደን ፓውል የተባሉ እንግሊዛዊ ናቸው ። ትምህርቱም የተጀመረው እንደ አውሮፓ አቈጣጠር በ፲፱፻፰ ዓ ም ነው ።

ዛሬ በመላው ዓለም ላይ ከፍ ያለ ጥቅምና አገልግሎት የሰጠው የስካውት ትምህርት እንግሊዛዊው ሎርድ ሮበርት የመሠረቱት ቀጥሎ በተመለከተው ምክንያተ ነገር ስለሆነ ሳናወሳው አናልፍም ።

በ፲፰፻፺፱ ዓ ም የዳች ወታደሮች በደቡብ አፍሪካ የሚገኘውን ማፌኪንግ የተባለውን የእንግሊዞችን ከተማ ወረረባቸው ። በዚያን ጊዜ የነበሩት የጦር ወታደሮች ሰባት መቶ ብቻ በመሆናቸው ፤ የከተማ ነዋሪዎችን ሁሉ ለወታደርነት መመልመል ግዴታ ሆነ ። ለአቅመ አዳም የደረሰ ማናቸውም ጕልማሳ ለወታደርነት ተመልምሎ በወታደርነት ተግባር ሲያገለግል ፤ የመላላክን ሥራ ልጆች እንዲሠሩ ተደርጎ በበይስካውት ሥራ እንዲሠለጥኑ ሆነ ።

ባደን ፓውል በዚያን ጊዜ የከተማ ጸጥታ ጠባቂ ወታደሮች አዛዥ ስለ ነበሩ ፤ ልጆች በበይስካውት ሥራ ትምህርት በሚያደርጉበት ቅልጥፍና ድፍረት እጅግ ተገረሙ ። ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ልጅ በተኩስ መካከል እየጋለበ አቋርጦ ሲመጣ አይተው ፤ መቸም አንድ ቀን በተኩስ መካከል ስትጋልብ ትሞታለህ ቢሉት ፤ እኔ ፈጣን ነኝ ተሽሎክልኬ አመልጣለሁ አይገሉኝም ብሎ መልስ ሰጣቸው ። ልጆች ለሕይወታቸው የማይሰሱ ቆራጥና ፍጹም የሆነ ያገር ፍቅር ያደረባቸው መሆናቸውን ባደን ፓውል ተገነዘቡ ።

ከዚህ በኋላ ባደን ፓውል በእንደዚህ ያለ ወታደራዊ ሥራ ልጆችን ማሠልጠንና ፤ የአገርን ፍቅር በሰፊው ተረድተው በአእምሮዋቸው እንዲቀረጽ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት የስካውትን ሥራ ለመመሥረት ለአሳባቸው ዓይነተኛ ምክንያት ሆነ ።

ባደን ፓውል ሰፊ በሆነው አስተያየታቸው በዘመኑ ደርሶባቸው በነበረው ጠባብ ችግር ተነሳስተው የመሠረቱት የስካውት ሥራ ዛሬ በዓለም ላይ እየተስፋፋ ከፍ ያለ አገልግሎት ሰጥቶ ይታያል ። ልጆችን ለጋ በሆነ ወጣት አእምሮዋቸው ላይ ፤ የአገር ፍቅርን ፤ ለማናቸውም ሰብአዊ ፍጥረት በጎ ነገርን የመሥራት ኃይል በሰውነታቸው ተዋህዶ እንዲያድግ ማድረግ ከሰው ላይ የሚፈለግ ታላቅ ተግባር ነው ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በተፈጥሮ በተሰጠው የዕውቀት ጸጋ የመንፈሳዊነት ትምህርት ከሁሉ በበለጠ የሚያፈቅር ሲሆን የስካውትነት ትምህርት ለመቀበልና ለመከታተል ከግብሩ ጋር የተዋሀደ ሥራ ስለሆነ ትምህርቱ እንግዳ ሊሆንበት አይችልም ።

በተፈጥሮ ካለው ዕውቀት ጋር አንድ አካል የሆነውን የስካውት ትምህርት በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መልካም ፈቃድና ትጋት በኢትዮጵያ በመጀመሪያ የተቋቋመው በ፲፱፻፳፪ ዓ ም በተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ የበላይ ጠባቂነትና መሪነት ነው ።


ለሰው ቀርቶ የፍጥረት ባሕርይ ላለው ሁሉ የርኅራኄ ሥራ መሠረት እንደ ሚገባ የሚጠይቀው የቦይስካውት ትምህርት በኢትዮጵያ በግርማዊነታቸው ታሪካዊ አስተያየት በጦር ቦይስካውት ሲመሠረት ፤ የበላይ ጠባቂነቱና መሪነቱ ርኅራኄ ፤ ጀግንነት ፤ ለራስህ ሊያደርጉልህ የምትወደውን አንተም ለሌላው አድርግለት የተባለውን ቅዱስ ቃል እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ዘመን ድረስ በመልካም ልባዊ ፈቃድ ሲፈጽሙ በኖሩት በተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን ተመሠረተ ። ይህ ድርጅት በልዩ ልዩ ዓይነት ተከፋፍሎና ተስፋፍቶ በመላ ኢትዮጵያ ዛሬ ግብሩን በሥራ ሲያሳይ ይታያል ።

የሰማያዊና የምድራዊ ገዥ መድኃኒታችን በዚህ ዓለም ራሱን አዋርዶ የትሩፋትና ታምራታዊ ሥራ ፤ ሠርቶ በመጠራጠር ላይ የነበሩትን ሁሉ ልባቸውን በፍቅር ማርኮ የርሱን ፈለግ ተከትለው የሚሠሩ ደቀ መዛሙርት አፈራ ።

ጌታችን በመለኮታዊ ግብሩ የርሱ ተከታይ ያደረጋቸው ደቀ መዛሙርት በሕይወታቸው ላይ የሚደርሰውን ፈተና ንቀው የተሰጣቸውን ትእዛዝ እመጨረሻው ግብ አድርሰው ሲያልፉ ስማቸው በሕይወት መዝገብ ተጽፎ ያስተማሩት ትምህርት ነዋሪ ሆኖ እነሆ ሲነገር ይኖራል ።

እንደዚሁም በተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን የበላይ ጠባቂነትና መሪነት በኢትዮጵያ በመጀመሪያ የተመሠረተው የጦር ቦይስካውት ፤ በዘመኑ አንድ ዓይነት ያገልግሎት ፍሬ ፤ ለአገሩ ያበረከተ ሲሆን በጠላት ወረራ ምክንያት ተቋርጦ የነበረው እንደገና ትንሣኤ አግኝቶ ፤ በሥራ የጠነከሩ ፤ በአእምሮ ዕውቀት የጐለመሱ ፤ የስካውትን ተግባር ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚያሸጋግሩ ቊጥራቸው የበዛ እስካውቶች አፍርተዋል ።

ይህ ከልዑልነታቸው የበላይ ጠባቂነትና የመሪነት ዕድል የተገኘ የሥራ ውጤት ስለሆነ ልዑልነታቸው በጦር ቦይስካውት ትምህርት ቤት የፈጸሙትን ተግባር በአጭር ስንገልጽ ፤ የስካውትን ድርጅት በማስፋፋት ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ የስካውት ማኅበር ለትውልድ በሚያቆያቸው የታሪክ ጽሑፎች ልዑልነታቸው ያስገኘውን ውጤት በበለጠ አስፋፍቶ እንደሚጽፈው በመተማመን ፤ "የታነጸ ድንጋይ የማዕዘን ራስ እንደሆነ" በኢትዮጵያ ለቦይስካውት ሥራ የማዕዘኑ ራስ ተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን መሆናቸውን ዘወትር ማስታወስ አለብን ።



ምንጊዜም በኀዘን የምናስታውሳቸው ተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ ።

የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ገዝሙ ፤ ጸሐፊ አቶ መኰንን የተመኙ ፤ ሞግዚት አቶ ከበደ ባልቻ ፤ መምህራን ሙሴ ጆርጅ የፈረንሳዊ ቋንቋና የሰልፍ ፤ የጤና ጥበቃ አስተማሪ ፤ አለቃ ወልደየስ አማርኛና ግብረ ገብ አስተማሪ ሙሴ ምሕሬ ፤ አናጢነት ሙሴ ማክሱት ፤ ጫማ ስፌት ያስተምሩ ነበር ፤ በዘመኑ የነበሩት ወጣቶች ከቀለም ትምህርት ጋር የእጅ ጥበብ ሥራ የአናጢነትና የጫማ ስፌት ይማሩ ነበር ።

በዚያን ጊዜ ይህን ትምህርት ለመማር ዕድል ካገኙት ዛሬ በአናጢነትና በጫማ ስፌት ሥራ ራሳቸውንና አገራቸውን የሚረዱ ወጣቶች ትምህርት ቤቱ ያበረከተ ስለሆነ ፤ ከልዑል መኰንን መስፍነ ሐረር ታሪክ ጋር የተያያዘውን የትምህርት ፡ ቤቱን አጭር ታሪክ ልናወሳው ወደድን ።

# የልዑል መኰንን መስፍነ ሐረር አጭር

## ታሪክና የኢትዮጵያ የጦር በይስካውት ት/ ቤት

በወጣትነት ላይ ይገኝ የነበረው የመድኃኔ ዓለም ትምህርት ቤት በግርማዊነታቸው ከፍ ያለ ፈቃድ በዘመናዊ የትምህርት ቤት አቅድ በሙሉ ድርጅት ከተዘጋጀ በኋላ በ፲፱፻፳፯ ዓ ም ትምህርት ቤቱ የኢትዮጵያ የጦር በይስካውት ትምህርት ቤት ተብሎ በወጣት መስፍን የበላይ ጠባቂነት እንዲመራ ዕድል አገኘ ።

መስከረም ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፯ ዓ ም በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መልካም ፈቃድ በልዑል መኰንን መስፍነ ሐረር ከፍ ያለ የበላይ ጠባቂነት የኢትዮጵያ ወጣቶች የጦር በይስካውት ትምህርት ቤት ተብሎ በተሰየመውና በቆመው ትምህርት ቤት ለመማር ዕድል ያገኙት ወጣቶች በበይስካውት ምልክት ያሸበረቀውን የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ከግርማዊነታቸው ተቀብለው ቃልኪዳን የሚገቡበት ቀን ስለነበር ፤ በዚሁ ቀን ልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ መስፍነ ሐረር በስምንት ሰዓት ተኩል የበይስካውት የማዕረግ ልብስ ለብሰው የተሰጡቸውን ሦስት መቶ ሰባ ስድስት ተማሪዎች በሰልፍ አዘጋጅተውና ራሳቸውም ተሰልፈው ለክብረ በዓሉ የተጠሩትን ክቡራን መኳንንት ፤ ሚኒስቴሮችና የውጭ አገር ሰዎች ሲቀበሉ ፤ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥት አልጋ ወራሽ ልዑል መርድ አዝማች አስፋ ወሰንን ሌሎችንም ልዑላን መሳፍንት አስከትለው ልክ ዘጠኝ ሰዓት በትምህርት ቤቱ ደረሱ ።

በተዘጋጀው ንጉሣዊ ሥፍራ ግርማዊነታቸው በቆሙ ጊዜ ፤ ሙዚቀኞች የኢትዮጵያን ሕዝብ መዝሙር በሙዚቃ ዜማ ሲያሰሙ የቀሩት ተማሪዎች የበይስካውትን ሰላምታ በመስጠት ተቀባበሉ ። ቃል ኪዳን ገብተው የሚቀበሉት

በቦይስካውት አርማ የተዘጋጀው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በግርማዊነታቸውና በተማሪዎቹ ፊት ለፊት እንደቆመ ፤ የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ቀጥሎ የተጻፈውን ንግግር አደረጉ ።

ግርማዊ ሆይ ።

ኢትዮጵያን ወደ ጓደኞቿ ለማድረስ ጉልህ ሐሳብዎ ስለሆነ በዘመነ መንግሥትዎ የሠሩላትን በጎ ሥራ ሁሉ ዘርዝሬ ልናገረው ወሰን የሌለው በመሆን መላው ሕዝብዎ ያውቀዋል በማለት ትቼ ለኢትዮጵያ በየጊዜው የሠሩላት የማይቆጠር ነዋሪ ሥራዎ ተጨማሪ ሆኖ በታሪክ ነገሥታትም የሚኖር ይህንን ተማሪ ቤት የመሠረቱበትን ነገር ከግርማዊነትዎ ፊት በተማሪቹ ስም ሆኜ እናገር ዘንድ ለኔ ለባሪያዎ ስለተፈቀደልኝ ለደስታዬ ወሰን የለውምና ለልዑላን መሳፍንትና ለክቡራን መኳንንት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን እናገራለሁ ።

ያለንጉሥ ነገሥት ኀብረት መቃፈር ያለ ነፃነት ሰንደቅ ዓላማና ክብር የማይገኝ መሆኑን ተረድተው ሲያስረዱን ፤ የኢትዮጵያን ሕፃናት ገንዘባቸው በመሆኑ ባርበኝነት ዕድላቸው ላይ የወታደርነትን ትምሕርት በመመገብ ለመጐልመስ ለሀገራቸው ነፃነት ተቆርቋሪ ንጉሠ ነገሥታቸውን አክባሪ ሁነው እንዲገኙ ለማድረግ ስመጥሩዋን አገራቸውንአርበኛውን ሕዝባቸውን ከመላው ዓለም ለማስተካከል ሲሉ እግዚአብሔር አብ ዓለምን ለማዳን ባሰበ ጊዜ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም እንደላከ እኛንም እስከ ፍጻሜ ዘመን የባዕድ ቀንበር እንዳይነካን ማናቸውንም በጎ ነገር ብቻማሰብ ሳይሆን ሠርቶ ማሳየት ዕድላቸው የሆነ ንጉሠ ነገሥታችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ ነፃነት ለዘለዓለም ጸንቶ እንዲኖር ፍጹም ሐሳባቸው መሆኑን ለመግለጽ ሲሉ ይህንን የቦይስካውት ተማሪ ቤት በግርማዊነታቸው ችሮታና ፈቃድ አቁመው በዓለም ስሙን ሰይመው በልዑል መኰንን መስፍነ ሐረር ጠባቂነት እንድንሠራበት ሰጡን ።

እኛ በአንድነት ከፊትዎ ቆመን የምንታይ የወደፊት የኢትዮጵያ ወታደሮች ባሮችዎ ከግርማዊነትዎ ለመመረጥ ሞገስ አግኝተን ጓደኞቻችን የኤሮፓ ሕፃናት እደረሱበት አደረሱን በትጉህ ጌታችን በልዑል መኰንን ጠባቂነት የተሰጠነውን ቃል ኪዳን አጽንተን ምኞትዎን እንድንፈጽም እያረጋገጥን በዘመነ መንግሥትዎ ኢትዮጵያና ሕዝቧ ምኞታቸው በትጋት በተፈጸመላቸው ጊዜ በመፈጠራችን ፈጣሪያችንን ከማመስገን አናቋርጥም ።

ልዑል መስፍን ሆይ ።

አርበኛውን ስመ ጥሩውን አያትዎን በስምና በግብር እንዲመስሉ የግርማዊ አባትዎ የጋለ ምኞት መሆኑን እናውቀው ዘንድ በስምና መልክ ተመስለው በመንበራቸው መቀመጥዎ ገልጾልናልና የኢትዮጵያን ነፃነትና ወሰንዋን ጠብቃ ባንዲራዋንና ንጉሠ ነገሥቷን ማክበር ከመንበራቸው ጋር ከአያትዎ የወረሱት ዕድልዎ ነውና ስመ ጥሩ ተብለው የተጠሩትን ግብር ለመምሰል መጣርዎን እዚህ የተሰበሰብነው ተማሪዎች ከተረኮቡን ቀን ጀምሮ በየበዓሉም ምሳ መጋበዝ እሥራችንም ላይ አዘውትረው እየመጡ በማተጋጋትዎ ከእኛ አለመለየ

ዝግጁ ሁኑ የሚል ያዋጅ ነጋሪ ቃል የተጻፈበትን ሰንደቅ ዓላማ ልዑል መኰንን መስፍን ሐረር ከሰልፉ ወጥተው ከግርማዊ አባታቸው እጅ በመታመን ተቀብለው ወደ ሰልፉ ተመለሱ ።



ተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን /ኃይለ ሥላሴ ከግርማዊ አባታቸው በቦይ ስካውት አርማ የተዘጋጀውን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በመታመን ሲቀበሉ

ልዑልነታቸውም ሰንደቅ ዓላማውን ከተማሪዎቹ ለአንዱ ሲሰጡ ሙዚቀኞች በሙዚቃ ፤ የቀሩት ተማሪዎች በዜማ ቀጥሎ የተጻፈውን የቦይስካውት መዝሙር ዘምረው ለተቀበሉት ሰንደቅ ዓላማ ሰላምታ ሰጡ ።

፩ኛ/ እኛ ያገር ልጆች በይስካውት ሆነን
በርትተን እንማር አርበኝነትን
ኢትዮጵያ ወጣች ከጨለማ ደይን
በኃይለ ሥላሴ ሥልጣኑ ብርሃን ።

፪ኛ/ ኢትዮጵያ ልጆች እንውጣ ወደላይ ወደላይ
ኢትዮጵያን ይዘን በንጹሕ ጠባይ
ጠላት ድንቊርናን ዳግመኛ እንዳናይ
በኃይለ ሥላሴ የሁሉ ሰው ጠቅላይ ።

፫ኛ/ እናት ኢትዮጵያ ላርበኞች ልጆችሽ
እጆችሽን ዘርጊ በቅን ወደ አምላክሽ
ለነፃነታችን ቀደሞ የማለልሽ
በኃይለ ሥላሴ ይጽና ቃል ኪዳንሽ ።

፬ኛ/ ኢትዮጵያ ልጆችሽ ሆኑልሽ መሰሪ
በይስካውት ተብለው ጠላትሽን መርማሪ
ከአርበኞችሽ ጋር እንድትታፈሪ
በኃይለ ሥላሴ ለዘለዓለም ኑሪ ።

ይህ መዝሙር ትንቢቱን የፈጸመ ስለሆነ አፈጻጸሙን ሳንገልጥ አናልፍም ። ለምሳሌ በአንደኛው ተራ ቍጥር «በርትተን እንማር አርበኝነትን» የተባለው አረፍተ ቃል በአምስቱ የጠላት ዘመን በሥራ ላይ ውሎዋል ።

በሁለተኛው ተራ ቍጥር “የኢትዮጵያ ልጆች እንውጣ ወደላይ ወደላይ„ የተባለው አረፍተ ቃል ዛሬ ኢትዮጵያ ያለችበትን የሥልጣኔና የኑሮ ደረጃ ያስታውሳል ።

በሦስተኛው ተራ ቍጥር “እናት ኢትዮጵያ ለአርበኞች ልጆችሽ„ የተባለው አረፍተ ቃል አገራችን ኢትዮጵያ በጠላት እጅ ወድቃ በነበረው ሰዓት ቸር እግዚአብሔር መዓቱን በምሕረት ለውጦ ያደረገልንን ታዳጊነት ያስገነዝባል።

መዝሙሩ እንደተፈጸመ ከተማሪዎቹ አንዱ እጁን በሰንደቅ ዓላማው ላይ ዘርግቶ ለኢትዮጵያና ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ታማኝ ሆኜ ለመኖር ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የሚያወጥዋቸውንም ሕጎች ለመፈጸም ቃል ኪዳን ገብቻለሁ ፤ ለዚሁም ረዳቴ እግዚአብሔር ይሁን ሲል ታመነ ። የቀሩትም ተማሪዎች ጓደኞቻቸው በማለው መሐላ ኅብረት እንዳላቸው እጃቸውን ወደ ሰንደቅ ዓላማው ዘርግተው ድምፃቸውን በጠቅላላው አሰሙ ።

ከዚህ በኋላ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሚከተለውን መሪ ቃል ተናገሩ ።

## የግርማዊነታቸው ንግግር ።

በዓለም ላይ የተፈጠረ ማናቸውም ነገር ሁሉ በመጀመሪያ ትንሽ እየሆነ በየጥቂቱ ወደትልቅነት ይደርሳል እንጂ ባንድ ጊዜ ትልቅ ሆኖ የሚገኝ



ተወዳጁ ፣ መስፍን ልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ ከግርማዊ አባታቸው ፣ በቦይስካውት እርማ የተዘጋጀውን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ለመቀበል ከስካውቶቹ ጋር እንደቆሙ ።

እንደሌለ የታወቀ ነውና እናንተም አሁን በመጀመሪያ ትምህርት ቤት ብትገቡ አባቶቻችን በዘመናቸው ያቆዩንን የጦር እውቀት በዘመናችን ባለው የጦር ሥራ ዕውቀት ወደፊት ከትልቁ የአርበኝነት ሥራ ደርሳችሁ አጥንታችሁን እስከ መከስከስ ደማችሁን እስከ ማፍሰስ ጸንታችሁ የአገራችሁን የኢትዮጵያን ነፃነት እንድትጠብቁ ሳስረዳችሁ ደስ ይላችኋል ። አሁን በለምለሚቱ እናታችሁ በኢትዮጵያ መሬት ላይ ስለዘራኋችሁ ቡቃያችሁ አምሮ ታይቷልና ደግሞ ዘር ዘርቶ ጠባቂ ካልተደረገለት አረም እንዲውጠው ስለተረዳነው የሐረር መስፍን ልጃችን መኰንንን በችግራችሁ ሁሉ እንዲረዳችሁና እንዲጠብቃችሁ አድርገናል ።

እንደዚሁም ቡቃያችሁ እያማረ ወደፊት አብባችሁና ፍሬአችሁን ለማየት እንድንበቃ እግዚአብሔርን እንለምናለን ። አሁን ልጆች በመሆናችሁ የተናቃችሁ ቢመስላችሁ እንኳን ፤ የተናቀው ድንጋይ የማዕዘን ራስ ሆኗልና ትምህርታችሁን ስትጨርሱ የአርበኝነት ስምና ሹመት እንድታገኙ ተስፋ አድርጋችሁ እንድትማሩ ብትሆኑ ለእኛም ለኢትዮጵያም ትልቅ ደስታ ትሆናላችሁ ።

የግርማዊነታቸው ንግግር እንደተፈጸመ ሦስት ወር ያህል ተማሪዎቹ ያደረጉት የሰልፍና የጦር ስልት ትምህርት ታየ ። በሦስት ወር ያሳዩት የጦር ዘዴ ትምህርት ተመልካቾችን አስደስቶ በልዑልነታቸው መሪነት የሚካሄደው ትምህርት ቤት ያደረገው አጭር የሥራ ፍሬ ከታዩ በኋላ ግርማዊነታቸው በመጡበት ሁኔታ በክብር ታጅበው ወደ ቤተ መንግሥታቸው ተመለሱ ።

ልዑል መኰንን መስፍነ ሐረር የተቀበሉትን ሰንደቅ ዓላማ በተዘጋጀለት ሥፍራ ከተማሪዎቹ ጋር ሆነው አስቀምጠው ወደቤታቸው ተመለሱ ።

ተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን በለጋውና በለመለመው ዕድሜያቸው ከተማሪዎቹ ጋር ተሰልፈው የፈጸሙትን አገልግሎት ተማሪዎቹ ሁሉ ሲያስታውሱት ልባቸው በኀዘን ይነካል ። በልዑልነታቸው የበላይ ጠባቂነትና መሪነት በኢትዮጵያ መጀመሪያ የተመሠረተው የበይስካውት ትምህርት በአዲሱ ዘመን በበለጠ እየተስፋፋ ሔዷል ።

የጥንት ነገሥታት ልጆች ከድሆች ልጆች ጋር በአንድ ትምህርት ቤት ገብተው የቀለም ጓደኛ አይሆኑም ነበር ፤ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በኢትዮጵያ የሥልጣኔ ብርሃን ሲዘረጉ ከአብራካቸው የተከፈሉ የሚወዷቸው ልጆቻቸው ከድሆች ልጆች ጋር በአንድ ትምህርት ቤት እንዲማሩ ማድረጋቸው ታላቅ አስተያየት ነው ።

የግርማዊነታቸው ታሪካዊ አስተያየት ልዑላን ልጆቻቸውን ከኢትዮጵያ ወጣቶች ጋር በጣም ያቀራረበና በፍቅር ያስተሣሠረ ስለሆነ ፤ እነሆ በተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን ሕፃናቱ ፤ ሽማግሌው ፤ ጐልማሳው ሳይቀር ሁሉም መሪር ኀዘን ተሰምቶት ዕንባውን እንደጐርፍ አፈሰሰ ።

ተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን እንዳንዱ ተማሪ የቦይስካውት ልብስ ለብሰው ከተማሪዎቹ ጋር ተማሪነታቸውን መግለጽ ብቻ ሳይሆን ፤ ይህን ዓለም በሞት ጥለውት እሔዱ ድረስ፥ በዚያን ጊዜ ከነበሩበት ተማሪዎች ጋር እንዳንዱ ተማሪ በማኅበራዊ ኑሮ ተሳስሮ ለመኖር የነበራቸውን በጎ ፈቃድ ስናስታውስ ምን ጊዜም ከልባችን ውስጥ ኀዘኑ አይጠፋም ።



ልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ የተሰጧቸውን የጦር ቦይስካውት ተማሪዎች አሰልፈው ቦይስካውት ሰላምታ ሲሰጡ ።

# ልዑልነታቸው በትምህርት ቤት

## ይፈጽሙት የነበረው መልካም አገልግሎት ።

ከግርማዊ አባታቸው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የተቀበሉትን የጦር ቦይስካውት ትምህርት ቤትና በትምህርት ቤቱ ይማሩ የነበሩትን ሦስት መቶ ሰባ ስድስት ተማሪዎች የዘገየ እንደሆነ በሳምንት አንድ ቀን በቀረ በሣምንት ሁለት ቀን በትምህርት ቤቱ እየተገኙ ተማሪዎቹ የጦርና በክፍልም ውስጥ የቀለም ትምህርት ሲማሩ እየጐበኙ ያበረታቱዋቸው ነበር ፤ በምግብ ጊዜም ልዩ ልዩ ጣፋጭ ፍራፍሬ ምግብ እያሲያዙ ከግርማዊ አባታቸው ጋር ከመምጣታቸውም በላይ ፤ በአንድ ገበታ ከተማሪዎቹ ጋር ይመገቡ ነበር ። ይህ የልዑልነታቸው ሰብአያዊ ርኅራኄ የተማሪዎቹን ልብ በፍቅር ማርኰት ለትምህርታቸው አወሳሰድ ብርታትና ጥንካሬ ሰጥቶ ነበር ።

ከብዙ በጥቂቱ ለማስረጃ የምንናገረው ለተማሪዎቹ አካል ብርታትና ጥንካሬ የሚሰጥ ልዩ ልዩ የሰውነት ማጠንከሪያ ትምህርት በትምህርት ቤቱ የሚሰጥም ቢሆን ፤ ቢሲክሊት የመንዳት ልምድ እንዲያደርጉና ሰውነታቸውንም ለሰውነት ደስታ በሚሰጥ መንፈስ እንዲያበረቱ ተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን አዲስ ቢሲክሊት ከትምህርት ቤቱ ድረስ አምጥተው ለተማሪዎቹ ሰጡ ። በቢሲክሊቱ ተማሪዎቹ ሁሉ ሲጠቀሙ ከዕለታት አንድ ቀን ዘለለው እንደሻው የተባለ ተማሪ (አሁን ሻምበል) ቢሲኪሊት ተቀምጦ ከትምህርት ቤቱ ውጭ ሲሄድ ወድቆ በጥርሶቹ ላይ አደጋ ደረሰበት ። ልዑል መኰንን መስፍን ሐረር ይህንኑ ሰምተው ፈጥኖ ደራሽ በመሆን ከትምህርት ቤቱ ድረስ መጥተው ተማሪውን ጠይቀው ከአነጋገሩት በኋላ ፤ በትምህርት ቤቱ ደንብ ከተደረገለት ሕክምና በላይ በበኩላቸው የገንዘብ ርዳታ አደረጉለት ፤ እንግዲህ ሰው የሆነ ለሰው ከዚህ በላይ ምን ሊያደርግ ይችላል ? ይህን ከመሳሰለ በጎ አድራጎታቸውም በላይ በዕረፍት ጊዜ በትምህርት ቤቱ እየተገኙ ከተማሪዎቹ ጋር ልዩ ልዩ ጨዋታ ያደርጉ ነበር ።


ከዚህም በቀር ከተማሪዎቹ ቤተ ሰቦች ፤ ችግር የደረሰባቸው ችግራቸውን በቅርብ ለሚያገኙዋቸው ልዑልነታቸው በመለከቱ ጊዜ ለግርማዊነታቸው አመ ልክተው ይፈጽሙት የነበረው ተግባር ለብዙዎች ችግረኞች ፈውስ ሁኑዋቸው ነበር ። ለተቸገሩ ማማለድና ትሩፋት ማድረግ ከልዑልነታቸው ጋር አብሮ ያደገ የተፈጥሮ ጠባይ ስለሆነ ከዚህ ዓለም በሞት እስኪተለዩ ድረስ በዚህ ተግባር የፈጸሙት አገልግሎት በጽሕፈት ሊነገር ስለማይቻል ሁሉም በየቤቱ ይመዝነው በማለት ቃልኗል ።

# የዛሬው የስዊድን ንጉሥ ።

የዛሬው የስዊድን ንጉሥ በ፲፱፻፴፯ ዓም በአልጋወራሽነታቸው ኢትዮጵያን ለመ ጐብኘት መጥተው በነበረ ጊዜ ፤ የእንግዳው የክብር ተቀባይ ተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን ነበሩ ። ልዑልነታቸው የኢትዮጵያን የክብር እንግዳ ለማስደሰት በል ዑልነታቸው የበላይ ጠባቂነት ይመራ በነበረው የጦር ቦይስካውት ትምህርት ቤት ይማሩ የነበሩት ተማሪዎች በልዑልነታቸው አማካይነትና መልካም መሪነት ለእንግ ዳው ሰልፍና ጂምናስቲክ አሳይተዋል ። በታየውም ሰልፍና ጂምናስቲክ ለኢትዮጵያ ታላቅ የክብር እንግዳ ለነበሩትና ለሌሎችም ተመልካቾች የደስታ ስሜት ፈጥሮ ወጣቱ መስፍን ልዑል መኰንን ለወደፊት ለኢትዮጵያ ዕድገት እጅግ ጠቃሚ መስፍን መሆናቸውን አመራራቸው መስክሮ ነበር ።

በልዑልነታቸው የበላይ ጠባቂነት ቃል ኪዳን የገቡት የመጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውት ተማሪዎች የፈጸሙት አገልግሎትና ትምህርት ቤቱ የፈጸመው ፍሬ ።

በግርማዊነታቸው ታሪካዊ ትጋት የተቋቋመው የጦር በይስካውት ትምህርት ቤት ሥራውን በኃለ መንፈስ ሲቀጥል ከፍተኛ ትምህርት የሚሰጥበት ሆለታ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የጦር ትምህርት ቤት ተከፈተ ።




ዛሬ የስዊድን ንጉሥ የሆኑት ኢትዮጵያን ለመጐብኘት መጥተው በነበረ ጊዜ የመጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውት ተማሪዎች በጦር መለማመጃ በትር ሰላምታ ሲሰጡ ።

በዚህ ከፍተኛ የጦር ትምህርት ቤት ገብተው ለመማር ዕድል የተሰጣቸው ከፍተኛ ትምህርት ያላቸው ወጣቶች ስለነበሩ ከበይስካውት የጦር ትምህርት ቤት ከፍተኛ ትምህርት ያላቸው ሃያ አምስት ወጣቶች በፈተና ተመርጠው ሆለታ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የጦር ትምህርት ቤት በመጀመሪያ ከተቀበላቸው ተማሪዎች ጋር የኢትዮጵያ የጦር በይስካውት ትምህርት ቤት ያበረከታቸው ወጣቶች ቅድሚያ በማግኘት ገብተዋል ።

አገራችን ኢትዮጵያ በተፈጥሮዋ ለምለም በአየርዋና በአቀማመጥዋ በጣ ቅላላ ተፈጥሮዋ ለሰው ልጅ መኖሪያ እጅግ የተወደደች ስለሆነች ከብዙ ዘመን ጀምሮ ነፃነቷንና ታሪኳን ደምስሶ በምድርዋ ለመጠቀም ሌት ከቀን እንቅልፍ

የሌላው የባዕድ አገር መንግሥት የረዥም ዘመን የጦር ድርጅት አድርጐ አገርዋን ለመውረር እንደተነሣ ሲታወቅ በልዑልነታቸው መሪነት ከሚማሩት የጦር ቦይስካውት አንድ መቶ ኻያ ተማሪዎች ለጦር ሥራ አሰልጣኝነት ተመረጡ ።



የመጀመሪያዎቹ የጦር ቦይስካውት ተማሪዎች ከከተማ ውጭ ወጥተው የጦር ልምምድ ለመማር ሙሉ ትጥቃቸውን ታጥቀው ሲዘጋጁ ።

ምርጫው የተፈጸመው በትእዛዝ ሳይሆን ተማሪዎቹ ባደረጉት ጥያቄ መሠረት ነው ፤ በገባነው ቃል ኪዳን ስለ አገራችን ነፃነትና ስለ ንጉሠ ነገሥታችን ክብር ደማችንን ለማፍሰስ ወደ ጦር ግንባር መሔድ አለብን ፤ ሲሉ ለትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ቢያመለክቱ የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ጥያቄያቸውን ለግርማዊነታቸው አመለከቱላቸው ።

ጥያቄው ምንም ከነርሱ ነቅቶ ቢቀርብ ዕድሜያቸው አይፈቅድላቸውምና ባሉበት ሁኔታ ትምህርታቸውን ይቀጥሉ ሲሉ ግርማዊነታቸው ትእዛዝ ሰጡ


ነገር ግን ተማሪዎቹ በጀግንነትና በቆራጥነት መንፈስ የተነሡ ስለ ሆነ አሳባቸውን እንደገና አስፋፍተው ለመሪያቸው ለልዑል መኰንን ኀይለ ሥላሴ ነገሩ። ልዑልነታቸው ጉዳዩን እንደገና ለግርማዊነታቸው አመልክተው በዕድሜ ከፍ ያሉት ለአሠልጣኝነት እንዲመረጡ ትእዛዝ ተሰጠ ። በትእዛዙ መሠረት ምርጫው ከተፈጸመ በኋላ ፤ ለጦር ሥራ አስተማሪነት ከበልጅግ አገር ከመጡት ጋር በታላቁ ቤተ መንግሥት ፊት ለፊት ጐተራ ሜዳ በሚባለው በግራዝማች አበራ ግዛው ዋና አዛዥነት ይተዳደር የነበረውን የክብር ዘበኛ ጦር ሲያሰለጥኑ ጥቂ

ቶቹ በሐረር ጠቅላይ ግዛት የተሰበሰበውን የጦር ወታደር ለማሠልጠን ወደ ሐረር ተላኩ ።

የተማሪዎቹ በዕድሜ ማነስ ቅር ያሰኘም ቢሆን የቀለም አባታችን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ተከትለን አገራችንን ለመውረር የመጣውን ጠላት ከአሠለጠናቸው የጦር ወታደሮች ጋር በጦር ሜዳ ተሰልፈንና የገባነውን ቃል ኪዳን ጠብቀን ግዳጃችንን መፈጸም አለብን እንጂ አንቀርም ብለው ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት በፈቃዳቸው ወደ ዘመቻው ተጓዙ ።

ርኅራኄ ምግባራቸው የሆን ግርማዊነታቸው ከደሴ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለሱ ትእዛዝ ሰጡ ። ነገር ግን የጦሩ ዋና አዛዥ ግራዝማች አበራ ግዛው አሠልጣኞቹ ከወታደሩ ተለይተው መቅረታቸው የሚያስከትለውን ችግር ከማመልከታቸውም በላይ በይስካውቶቹም የመመለስ ፈቃድ'እንደሌላቸው አስታወቁ።

በአሳባቸው ጸንተው ስለአገራቸው ነፃነትና ስለንጉሠ ነገሥታቸው ክብር በማይጨው ጦር ሜዳ ደማቸውን አፈሰሱ ።



የመጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውት ተማሪዎች ከከተማ ውጪ የጦር ልምምድ ትምህርት በሚያደርጉ በት ጊዜ የሥፍራውን ሁኔታ በካርታ ሲያመሳክሩ ።

በጦር ሜዳ ከዋሉትም ስልሣው በጀግንነት ሲዋጉ ተሠዉ። የኢትዮጵያ ጀግኖች በቆራጥነት መንፈስም በኃይል ምንም ቢከላከሉ ከስልሳ ዓመት በፊት በኢትዮጵያ ጀግኖች ጕራዴ አንገቱ የተወራረደው ጠላት በእግረኛ ጦር ግንባር ለግንባር ደረት ለደረት ገጥሞ ለመከላከል እንደማይችል አውቆ በአየር እያንዣበበ በመርዝና በቦምብ ኃይል ለጊዜው በወራሪነት አገራችን ከገባ በኋላ የጦር ትምህርታቸውን በበለጠ ለመቀጠል ከጦር በይስካውት ትምህርት ቤት በጦርነቱ ሰዓት ሆለታ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የጦር ትምሕርት ቤት በግርማዊነታቸው ፈቃድ ሔደው የነበሩት የጦር በይስካውት ተማዎሪች ከልዑል ራስ እምሩ ጋር በምዕራብ ወለጋ በተደረገው የአኤሮፕላን ቃጠሎና እንደዚሁም በጌራ በሆነው ታላቅ ጦርነት የጀብዱ ሥራ ሠርተዋል ።

ከዚህም በቀር ስለአገራቸው ነፃነትና ስለ ንጉሠ ነገሥታቸው ክብር በአምስቱ የጠላት ዘመን ከጠላት ጋር በአርበኝነት ሲዋጉ የሞቱትን ሳናስታውሳቸው አናልፍም ።

በማይጨው የጦር ሜዳ ደማቸውን አፍስሰው በእግዚአብሔር ቸርነት ሕይወታቸው የተረፈው በአምስቱ የመከራ ዘመን በአዲስ አበባ ልዩ ልዩ ግፍ እየተቀበሉ ቢቀመጡም ስለአገራቸው ነፃነትና ስለንጉሠ ነገሥታቸው ክብር እጅግ መሪር በሆነ የኀዘን ጦር ልባቸው ተወግቶ በኀዘንና በጸሎት አልተለዩም ነበር ።

ይህንንም ለማረጋገጥ የበንዲራ ማርያም የተባለ የቆሎ ማኅበር አቋቁመው በወር አንድ ጊዜ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በምትውልበት እየተገናኙ ስላአገራቸው ነፃነትና ስለንጉሠ ነገሥታቸው ክብር በጠቅላላው ስለ ኢትዮጵያ ዕድል ከሕሊና የሚመነጭ ጸሎት ያደርጉ ነበር ። ልባዊ በሆነ የሐዘን ስሜት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ያሳሰቡት የነበረውም ዓለምን ለማዳን የሰው ፍቅር አገብሮት ወደዚህ ዓለም ሲመጣ ከሴቶች ሁሉ አንቺ የተመረጥሽ ቅድስት ድንግል ንጽሕት ሆነሽ በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከአንቺ ከተወለደ በኋላ በሄሮድስ ምክንያት ሕፃኑን ታቅፈሽ ወደ ምድረ ግብፅ በተሰደድሽ ጊዜ በመንገድ ላይ የደረሰብሽን መንገላታት ፤ በስደት በሰው አገር እንደምን ያለስሜት በልብ ውስጥ እንደሚፈጠር ታውቂዋለሽ ።

ይልቁንም ረኀቡን ጥማቱን ሁሉንም ያየሽው ስለሆነ ሃይማኖታችንን ለማጥፋት ታሪካችንን ለመደምሰስ በግፍ የተነሣብን ጠላት አገራችንን ወርሮ ሕፃናቱን አሮጊቶችንና ሽማግሌዎችን በግፍ እየገደለ አገራችን በልጆቿ ደም ታጠበች ፤ ንጉሠ ነገሥትዋ ነፃነትን ለማስመለስ በስደት በሰው አገር ይንከራተታሉ ። ነፍሳቸውን ለእግዚአብሔር ሥጋቸውን ለመከራ ሰጥተው በየገዳማቱ በመንፈሳዊ ተግባር ተጠምደው የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆኑት ሁሉ በበአታቸው ውስጥ እንዳሉ በሞት ተደበደቡ ፤ ይህን ሁሉ ግፍ በመመልከት በእ

ጠባሽው ጡትሽ በጀርባሽ አዝለሽ በምድረ ግብጽ በስደት የፈጸምሽውን መንከራተት ሁሉ በማዘከር የአገራችንን ጠላት ታምራታዊ በሆነ ሥራው አጥፍቶ ነፃነታችንንና ንጉሠ ነገሥታችንን እንዲመልስልን አማልጅን ፤ ይህን በቆሎ የጀመርነውን ማኅበር ነፃነታችን ከተመለሰ በኋላ አቅማችን በሚፈቅደው መጠን አስፋፍተን በስምሽ ለተራቡና ለተጠሙ ድሆች እንመግባለን ብለው ብጽዓት አድርገው ነበር ።

የለመኑትን የማይነሳ የነገሩትን የማይረሳ እግዚአብሔር መዓቱን በምሕረት ለውጦ ነፃነታቸውን ለማግኘትና ንጉሠ ነገሥታቸውን ለማየት ቻሉ ። ከመሬው ተመሬው እንደሚባለው ይህ ዓይነት የመንፈስ ብርታት በተማሪዎቹ ላይ ሊያድር የቻለው ተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን በሰላማዊው ጊዜ በሕፃንነት ዕድሜያቸው በተማሪዎቹ ላይ ያሳደሩት ፍቅር በያንዳንዱ ተማሪ ልብ ስለተቀረጸ ነው ።

በሰላማዊ ጊዜ ሰላማዊ መስለው አገራችን ያፈራችውን እየተመገቡ ከድህነት ወደ ብልጽግና ደረጃ ከተላለፉ በኋላ ፤ የተንሡበትን የኑሮ ደረጃ እየረሱ አገርዋን ለማጥቃት ከሚነሣ ጠላት ጋር አበሬ እየሆኑ ጉዳት የሚያደርሱ በውስጣችን የሚገኙ የሰው አገር ሰዎች መሆናቸውን አንዘንጋ ።

ሙሴ ፍሬዴሪክ የተባለ የጦር ቦይስካውት አስተማሪ የጠላት ሰላይ ሆኖ ከታሰበውና ከታቀደው በላይ የጠላትን ኃይል በማጋነን የተማሪዎችን ልብ የሚያሸብር ወሬ እያወራ መጥፎ መንፈስ በተማሪዎች ላይ ይዘራ ነበር ።




የመጀመሪያዎቹ (ጦር ቦይስካውት ተማሪዎች ፤ ከከተማ ውጪ ወጥተው የጦር ልምምድ በሚያደርጉበት ጊዜ በዛፍ ጠለላ የጦር ውጊያ ትእዛዝ ሲቀበሉ ።

ሰላይ መሆኑን ተማሪዎቹ ተከታትለው ከደረሱበት በኋላ በነሱ አሳሳቢነትና በአስጨበጡት ማስረጃ መሠረት ከአገር እንዲወጣ ተደረገ ።

ይህን ተግባር የፈጸሙት በዕድሜያቸው ዝቅተኛ ሆነው ወደ ጦር ግንባር ሳይሄዱ በትምህርት ቤቱ ትምህርታቸውን ይከታተሉ የነበሩት ተማሪዎች ናቸው ።

ግርማዊነታቸው ካርቱም እንደገቡ ከጦር በይስካውት ተማሪዎች አንዱ አቶ መኰንን ደስታ ከግርማዊነታቸው ተገናኘ ። ቀጥሎም ከልዑል መኰንን መስፍነ ሐረር ጋር ተገናኝቶ አሳብ ለአሳብ ከተለዋወጠ በኋላ ፥ በትምህርት ቤት የገቡትን ቃል ኪዳን በማስታወስ በጀመረው አገልግሎት ጠንክሮ መልካም ውጤት እንዲያሳይ የሚያበረታታ ቃል ነገሩት ።

ከዚህ በኋላ የግርማዊነታቸውን በድል አድራጊነት መምጣት የሚያበስር የዐዋጅ ቃል ተቀብሎ በበላይ አድርጎ በጐጃም ስለአገራቸው ነፃነትና ስለንጉሠ ነገሥታቸው ክብር በአርበኝነት ለሚዋጉትና ለሌላውም የግርማዊነታቸውን መምጣት በተስፋ ለሚጠባበቀው ሁሉ የዐዋጁ ቃል በመበተን አገልግሎቱን ፈጽመዋል ።



የመጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውት ተማሪዎች በድምፅ ግንኙነት ለማድረግ በማይቻልበት ጊዜ ጨርቅ በማውለብለብ ንግግር ሲቀባበሉ ።

ጐጃም ከደረሰም በኋላእንደ ገና በሸዋና በደራ በቦረና ላሉት አርበኞች እንደዚሁ የግርማዊነታቸውን መምጣት እያስተላለፈ መልካም አገልግሎት የፈጸመው የጦር በይስካውት ትምህርት ቤት ተማሪ ነው ።

ልዑል መኰንን መስፍን ሐረር በስደት ላገኙት የጦር በይስካውት ተማሪ ያደረጉት ማጽናናት የመንፈስ ኃይል ሰጥቶት የጊዜው ፖለቲካ ሳይፈታው አገልግሎቱን ከመጠረሻው ግብ አድርሷል ። ይኸውም ከልዑልነታቸው ትጋትና የሥራ ፍሬ የተገኘ ውጤት ነው ።

በፍቅር ሰውን መማረክና ለሰው በጐ ነገር መሥራት ለሠሪው ቀላል ለተሠራለት ግን እጅግ ከባድ ነው ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕርዩ መሞት የማይገባው ከመሆኑም በላይ ፤ ዓለምን ዞሮ አስተምሮ በደዌ ሥጋ ይሰቃዩ የነበሩትን ፈውሶ ፤ የሞቱትን አሥንስቶ ለሰው ልጅ ያደርገው የነበረው ታላቅ ታምራታዊ ሥራ አልበቃ ብሎ በመስቀል ተሰቅሎ የሞተው ሰውን በፍቅር ለመማረክ ሲል ነው ። ይኸውም አድራጎት ዓለም ዘለዓለም እየተነገረ የሰውን ልብ በፍቅር ሳበ ።

እንደዚሁም ተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን በአጭሯ የሕይወት ዘመናቸው የፈጸሙት በጐ ሥራ በሞታቸው ጊዜ ተገልጾ ታሪካቸውን እያገነነ ሲያናግር ይኖራል ።

# ተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን

## በስደት አገር ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የጦር ሠራዊታቸውን ልከው ማዋጋት ብቻ በቂ መስሎ ስላልታያቸው ራሳቸው ከጦር ሠራዊታቸው ጋር እንደ አንድ የጦር ወታደር በጦር ሜዳ ተሰልፈው በማይጨው ጦር ሜዳ ከፍ ያለ የጀግንነትና የጀብዱ ሥራ ከሠሩ በኋላ በመርዝና በቦምብ የጦር ሠራዊታቸው ጉዳት እንደደረሰበት ተመልክተው ፤ ለአገራቸውና ለሕዝባቸው መዳኛ የሚሆን ድል የሚገኝበትን መንገድ ለመፈለግ ወደኤውሮፓ ሲሄዱ ተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን ከግርማዊ አባታቸውና ከግርማዊት እናታቸው ጋር በለንደን ቆይተዋል ።

የሰው ልጅ የተስፋው ምንጭ ተቆርጦ ፤ ራሱን ለመርዳት ብቻ ሰውነቱን በአዋረደበት በመከራ ጊዜ ፤ ልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ ተስፋ በለመቁረጥ ልበ ሙሉ ሆነው የአገራቸው ነፃነት ሲመለስ ለሕዝብ አስተዳደር የሚጠቅማቸውን ልዩ ልዩ የሆነ ዕውቀት ለንደን በሚገኘው « ደሊንግተን " ከተባለው ኰሌጅ ገብተው በመማራቸው ከፍ ያለ ዕውቀት አግኝተዋል ።

የሰው መንፈስ ትምህርትን ያህል ነገር ለመጨበጥ የሚችለው በአንድ በተደላደለ መንገድ ቆሞ ከልብ በሚያደርገው የአእምሮ ኃይል ነው ። ሰው ከአሳቡና ከመንፈሱ ጋር ባልተዋወቀበት ጠቅላላ ሕይወታዊ ኑሮው በመከራ ማዕበል ተውጦ ፤ የብስጭትና የትካዜ ጐሬ በሆነበት ጊዜ በትምህርት ቤት ገብቶ መማር የልዑልነታቸውን ከፍ ያለ የመንፈስ ብርታት የሚያሳይ ነው ።

ተስፋ ባለመቍረጥ በእግዚአብሔር የታመነ ሰው ዋጋውን እንደማያጣ ፤ ልዑል መኰንንም የኢትዮጵያን ትንሣኤ ለማየት በቅተው በወገኖቻቸውም ዘንድ መታሰቢያው የማይጠፋ ታላላቅ ሥራ ሠርተው የአዳም ልጅ በተራ የሚፈሩትን የሞት ጽዋ ተቀብለው በአካለ ሥጋ በሞት ሲለዩ ፤ በመንፈስ ግን የተለያቸው የለም ።

# ተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን

## ከለንደን ወደ ካርቱም ከሱዳን ወደ እናት አገራቸው ኢትዮጵያ ።

በኢትዮጵያ ተርከፍክፎ የነበረው የመከራ ዝናም በደስታ የፀሐይ ብርሃን አሸብርቆ ፤ የነፃነት ፋና በግርማዊነታቸው እያበራ እንኳን ሰው ፤ እንስሳና የዱር አራዊት በየቋንቋቸው ለእግዚአብሔር ምስጋና የሚያቀርቡበት ቀን በደረሰ ጊዜ ልዑል መኰንን መስፍነ ሐረር ከግርማዊነታቸው ጋር ከለንደን ወደ ካርቱም ተጓዙ ።

ግርማዊነታቸው በሱዳን የጦር ሠራዊታቸውን ሲያደረጁ ልዑል መኰንን መስፍነ ሐረር ካርቱም በቅዱስ ጊዮርጊስ የጦር ትምህርት ቤት ከእንግሊዝ የጦር መኰንኖች ጋር ለመታደር የሚያገለግላቸውን የጦር አቅድና ስልት ተማሩ ። የጦር ትምህርታቸውን ከጨረሱ በኋላ ፤ በሱዳን በኩል ለተሰለፈው ለኢትዮጵያ ጦር ለአንደኛው ክፍል አዛዥና መሪ ሆነው የበረሃ ዘመቻ በተባለው እጅግ ኃይለኛ ጦርነት ከግርማዊ አባታቸው ሳይለዩ በጀግንነት ተዋጉ ።

የጠላት ኃይል እየደከመ በግርማዊነታቸው የሚመራው የኢትዮጵያ ጦር ኃይል እያገኘ በአሸናፊነት ጐጃም ደብረ ማርቆስ ግርማዊነታቸው በድል ዘንባባ ታጅበው ገቡ ። ወደዚያው ወጣቱ መስፍን ልዑል መኰንን ባደረጉት ጀግንነትና ባሳዩት የጦር አመራር ከምስጋና ጋር የሜጀር ጀኔራልነት ማዕርግ አገኙ ።

መድኃኒታችን የሰውን ልጅ ከመርገመ ፍዳ በቸርነቱ ነፃ ለማውጣት ፈቃዱን ሲገልጽ ፤ ከስማየ ሰማያት መርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ የማዳኑን የምስራች ቃል ያናገረው በመላኩ ቅዱስ ገብርኤል አድሮ ነው ።

ከአምስት ዓመት ስደት በኋላ ግርማዊነታቸው በድል አድራጊነት የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በአሜድላ ሰቅለው ፤ ጐጃም ደብረ ማርቆስ እንደገቡ ፤ በጠላት አገዛዝ ለተሰቃየውና የግርማዊነታቸውን ገጽ ለናፈቀው ለተወዳጁ የአ

ዲስ አበባ ከተማና የሐረር ጠቅላይ ግዛት ሕዝብ የግርማዊነታቸውን ጉዳም ደብረ ማርቆስ በድል አድራጊነት መግባት ያበሰሩት ልዑል መኰንን ናቸው ።

ከጠላት ጋር የተፋፋመ ጦርነት ይደረግበት በነበረው ሰዓት በአሥራ ሰባት ዓመት ዕድሜ የምሥራች ነጋሪ ሆኖ መላክ የልዑልነታቸውን ወታደራዊ ጀግ ንነት ያሳያል ።

የልዑልነታቸው የምሥራች ነጋሪነት ጠላትን እየተከታተሉ ለማጥቃት በጀ ግንነት ይዋጉ ለነበሩት አርበኞች የበለጠ ኃይልና ብርታት ሰጥተዋቸው በነበ ራቸው ጀግንነት ላይ የበለጠ ጀግንነት ጨምሮላቸው ነበር ።


## ዘመን በዘመን ተለወጠ ።

መከራና ደስታ በሰው ልጅ ላይ በዘመን እየተፈራረቁ ስለሚኖሩ በኢት ዮጵያ ወድቆ የነበረው መከራ ተወግዶ የደስታ ዘመን ተተካ ። የሞተውንና በሕይወት ያለውን ወገን ማስታወስ ተገቢ በሆነበት ሰዓት ልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ የሞቱትንና በሕይወት ያሉትን የመጀመሪያዎቹን የጦር በይስከውት ተማ ሪዎች ጠየቁ ።

ለጊዜው ታውቀው በሕይወት ያሉትና በሞትም የተለዩት ከተነገራቸው በኋላ ፣ በሕይወት ያሉት የሚገናኙበት ራሱን የቻለ ቀዋሚ ማኅበር እንዲቋቋም አስፈላጊ መሆኑን አስገንዝበው ፣ በጦር ሜዳ ለወደቁት መታሰቢያ ፤ በጦር ሜዳ ለቈሰሉት ሊሻን እንዲያገኙ ለግርማዊነታቸው እንደሚያመለክቱ ለተማሪ ዎቹ ገለጹላቸው ። ከዚህም በቀር መንግሥት ከሚያዝበት መሬት ኵታ ገጠም ከግርማዊነታቸው ለምነው ፣ የመሬቱን ማቅኛ ገንዘብ ከራሳቸው ወጪ አድር ገው መሬቱ ከለማ በኋላ ፤ በገንዘባቸው ትምህርት ቤት አቋቍመው መታሰቢያ ነቱ የማይጠፋ ታላቅ ሥራ ለመሥራት ያላቸውን የሥራ ድርጅት አስረድተው፤ ማኅበሩ የሚቋቋምበትን የውስጥ ደንብ የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር የነበሩት ቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ገዝሙ ተማሪዎች ከነበሩት ከክቡር ብርጋዴየር ጄኔ ራል ዓቢይ አበበና ከደጃዝማች ብርሃነ መስቀል ወልደ ሥላሴ ጋር አዘጋጅ ተው እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ሰጡ ። በዚሁ ማኅበር ልዑልነታቸውም እንደአንዱ ተማሪ ማኅበርተኛ ለመሆን ፈቃድ እንዳላቸው ጨምረው ተናግረው ነበር ።

እንግዲህ አንድ መስፍን በትምህርት ቤት የነበረበትን ዘመን ወደኋላ አስ ታውሶ ከነበሩት ተማሪዎች ጋር በማኅበራዊ ኑሮ ተሳስሮ ለመኖር ፈቃዱን የሚ ያሳይ ይገኛል ? ።

በውነቱ የልዑል መኰንን በሞት ከዚህ ዓለም መለየት እጅግ አድርጐ የሚያ ሳዝነውና ከየንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሕሊና ኀዘኑ ሊጠፋ ያልቻለው በሕይወታቸው በሠሩት ደግ ሥራቸው ነው ።



የመጀመሪያዎቹ የጦር ቦይስካውት ማህበር የሚቋቋምበት ደንብ እንዲዘጋጅ ተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን በእጅ ጽሕፈታቸው ትእዛዝ ሰጡ ።


ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ከፍ ይላል፤ራሱን ከፍ የሚያደርግ ዝቅ ይላል እን ደተባለው ፤ ልዑል መኰንን መስፍነ ሐረር ራሳቸውን ዝቅ አድርገው የፈጸሙት ልዩ ልዩ መልካም ሥራ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ በፍቅር ማርኰ በሞት አሁን ሲለዩ ደግ ሥራቸውና ፍቅራቸው በያንዳንዱ ሰው እየታወሰ ፤ መሪር የሆነ የኀዘን ስሜት ጣለ ።

የመጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውቶች ተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ ለማኅበሩ ፕሬዚዳንት ሆነው ሁሉም በማኅበራዊ ኖሮ ተሳ ስረው እንዲኖሩ የነበራቸውንና በየጊዜው የገለጡትን መልካም አሳብ ሲያስታ ውሱት ለኀዘናቸው ማጽናኛ የሚሆን ነገር አላገኙም ።

# የልዑል መኰንን ኀይለ ሥላሴ መስፍነ


## ሐረር ዜና ዕረፍት ።

ተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን መስፍነ ሐረር ርኅራኄ ደግነትና ቸር ነት ባሕሪያቸው ሆኖ ለራስህ ሊያደርጉልህ የምትወደውን አንተም ለሌላው አድርግለት የተባለውን ተግባር ለወገኖቻቸው በመፈጸም ላይ እንዳሉ ፤ ሞት ጨካኙ ከመካከላችን ለይቶ በድንገት ወሰደብን ።



ተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ ግንቦት ፱ ቀን ፲፱፻፵፱ ዓ ም በአደጋ ምክንያት ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩባት ምድረ ርስት ።


የመጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውቶች ኀዘናቸውን ከመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የተካፈሉም ቢሆን ፤ ልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ ከአሥራ አንድ ዓመት ዕድሜያቸው ጀምሮ በቅርብ ሆነው የችግራቸው ተካፋይ በመሆን ያደረጉላቸው እጅግ የበዛው መልካም ሥራቸው በፊታቸው ውል እያለ ይታያቸዋል ።



በለ ተወዳጁ መስፍን የሰላሳኛ ቀን መታሰቢያ የመጀመሪያዎቹ የኢትዮጵያ የጦር በይስካውቶች በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ከጥዋቱ በአንድ ሰዓት ተገኝተው የፍትሐቱን ሥነ ሥርዓት ካስፈጸሙ በኋላ በበይስካውት አርማ ምልክት / የተዘጋጀውን የአበባ አክሊል ይዘው በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ከዞሩ በኋላ ወደ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሲያመሩ ።

የንጉሠ ነገሥት ልጅ ከፍ ባለ የመስፍን ደረጃ ላይ የሚገኝ ፤ ከድሆች ልጆች ጋር በማኅበራዊ ኑሮ ለመኖር ማነው ፈቃዱን የሚገልጥ ። ?


በያንዳንዱ ተማሪ ላይ ችግር ሲደርስ ፤ ፈጥኖ ደርሶ ፤ የድሆችን ችግር በቀና መንፈስ የሚቀበልና እንደጉዳዩ አቀራረብ የችግርን ቀንበር የሚያቃልል ማነው ? ይህ ዓይነት ሰብአዊ ርኅራኄ ያለው መስፍን በወጣትነት ዕድሜ በሞት ሲቀጭ እንዴት አያሳዝነንም ? እንዴትስ እንጀትን አይበላም ? ።



የመጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውቶች ስለመሪያቸው ልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ የሰላሳኛ ቀን መታሰቢያ ያዘጋጁትን የአበባ አክሊል በሰልፍ ይዘው ልዑል ራስ መኰንን ድልድይ እንደደረሱ ።

የመጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውቶች ኃዘናቸው የተከፈለላቸው መስሎዋቸው የልዑልነታቸውን ፴ኛ ቀን ምክንያት በማድረግ የአበባ አክሊል በመቃብራቸው ላይ ሲያስቀምጡ በአጭር የተዘጋጀ ድርሰት አበርክተዋል ።

ከመናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን እስከ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የተደረገውን ሥነ በዓል የሚገልጹ ፎቶ ግራፎች በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ ይገኛሉ ፤ የአበባ አክሊሉን በመቃብሩ ላይ ሲያስቀምጡ የሚከተለውን ንግግር አድርገዋል ።




መጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውቶች የአበባውን አክሊል በክብር ይዘው ወደ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ሲገቡ ።

አንተ የይሁዳ አንበሳ ደቦል ።

ያን ሁሉ ታሪክህን ፤ ደግነትህን ፤ ርኅራኄህን ፤ ጀግንነትህን ፤ ትክ ናንበህ ዛሬ በዚች መክነ ሙታን አጻራሽ እንደ አንበሳ ብቸኝነትህን መር

ጠሀ ፤ ከምትወዳቸው ከሚወዱህ ቤተ ሰብህና ከኢትዮጵያውያን ሕዝቦችህ ተለይተህ ፤ ያን ሁሉ ታዳጊነትህን ፤ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ የጣልክባቸውን የፍቅርና የታዳጊነት ዘውድ እንደ ዋዛ ነገር ቆጥረህ በዚች ጠባብ ማጥን ውስጥ ተንተርሰኸው ተኝተሃል ።



የመጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውት አስተማሪዎችና እስካውቶች በአስከሬኑ ላይ የኅሊና ጸሎት ሲያ ደርሱ።

ልዑል ጌታችን ሆይ ።

አባክህን ምን ይሆን ምክንያቱ ? ያስከፋህና የተከፋህበትስ ምን ይሆን ? ። በጦር ሜዳ በክፉ በስደትና በመከራ ቀን ያልተለየኻቸውን ግርማዊና ግርማዊትን ልዑላን ቤተሰቦችህን ተለይተኻቸው በአንድ ገዳም ውስጥ ለመኖር የመረጥከው ?

የተከፋህበት ነገር ገጥሞህ ይሆን ? ርኅሩኅ ፤ ጀግና ፤ ቸር ፤ ጌታ ፤ አስተዋይና ደግ ልዑል ፤ ታዳጊ መስፍን የወላጆቹንና የወዳጆቹን ፤ የአሽከሮችህን ፤ ልብ በኀዘን ጦር በድንገት ወግቶ መሔድ የመስፍን ተገቢ ሥራ ነውን ?



ከመጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውቶች አንዱ የመስናበቻ ቃል ሲያነብ የቀሩቱ በሐዘን ስሜት ተውጠው እንባቸውን በማፍሰስ ሲያዳምጡ ።

ዛሬ ከአስከሬንህ ፊት አገልጋዮችህ ቆመዋል ፤ ከብሩህ ገጽህና ከታዳጊው ሰውነትህ ስንብት ይጠይቃሉ ማን መልስ ይስጣቸው ? ማንስ ያሰናብታቸው ?

እንደበትህ ተይዟል ። ለችግረኞች መብራት የነበሩት ዓይኖችህና ለአሽከሮችህ ምርኩዝ የነበሩት እጆችህ የአዳም ዕዳ ሆኖባቸው ቸል ብለው አርፈዋል ።

ያ ርኅሩህ ጌታ ቆራጥ መኰንን
ታዳጊው ወታደር ጨካኙ መስፍን
እንዲናፍቁት ሲል እህት ወንድሙን
ልዕልት ባለቤቱን ልዑላን ፣ ልጆቹን
ታማኝ የሆኑትን ወዳጅ አሽከሮቹን ።
ካንድ ገዳም ገብቶ ያለ ወትሮ ልምዱ
ጨክኗል መስሎናል ዛሬስ ዛለ ክንዱ ።
ወረደብን ቊጣ በታተነን መብረቅ
ችግር ደረሰብን አፋጠጠን ጭንቅ
ሽሽቶ ተደበቀን ጌታችን ማናውቅ ።
በል በደህና ሰንብት ልዑል ለብቻህ
ተከታይም የለው ለበጐ ሥራህ ።

ዛሬ የአገልጋዮችህ የመጨረሻ መሰናበቻ ቀናቸው ነው ። አሰናብታቸው! አሰናብታቸው በነፍስ ሕያው ሁን ፤ ልዑል ጌታችን ሆይ ። አገልጋዮችህ የመ ጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውቶች ።

ንግግሩ እንዳለቀ ቀድሞ በትምህርት ቤቱ ለመለማመጃ ተብሎ ይማሩበት የነበረውን የበይስካውት በትር በጥቍር ቱቢት እንደ ተጠቀለለ ለመታሰቢያ ይሆን ዘንድ ከአበባው አክሊል ጋር በአስከሬኑ ላይ አስቀምጠው በበይስካውት ደንብ ሰላምታ ሰጥተው ተመለሱ ።

እንደዚሁም በቀጥታ ወደ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ሄደው ከግርማ ዊነታቸው ጋር ተገናኝተው የኀዘን ስሜታቸውን ገልጠዋል ።

በዚሁም ጊዜ ላደረጉት ንግግር ልባዊ በሆነ የኀዘን ስሜት ቀጥሎ የተጻ ፈውን ግርማዊነታቸው ተናገሩ ።


## የግርማዊነታቸው ንግግር ።

በሕይወት ሳለ እንዳልከዳችሁ ታውቃላችሁ ። እናንተም ውለታ ቢሶች አይ ደላችሁም ። ደስ የሚያሰኝ ሥራ ሠርታችኋል። እንደምታውቁት መሬት እንዲሰ ጣችሁ አስታውሶ በጉዳዩ በመነጋገር ላይ እንዳለ፤ ከአዳም በወረሰው ሞት ተለየን ። ምንም ርሱ በሞት ቢለየን ርሱ የጀመረውን ከፍጻሜ እናደርስላችኋለን ብለው በተ ናገሩ ጊዜ የሁሉም ልብ በኀዘን ጦር ተወግቶ እንባቸውን አፍስሰው ተመለሱ።

ወደዚያው ወደ ተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን መኖሪያ ቤት ሔደው ከልዕልት ባለቤታቸው ጋር በመገናኘት ኀዘናቸውን ከገለጡ በኋላ በዚሁ መጽ ሐፍ የሚገኘውን ፎቶግራፍ ለመታሰቢያ ከልዕልት ሣራ ግዛው ጋር ተነሱ ። ቀጥሎም በልዑል አልጋ ወራሽና በልዑል ፣ ሣህለ ሥላሴ መኖርያ ቤት ሔደው የተዘጋጀውን ድርሰት አበርክተዋል ።

# የመጨረሻ መሰናበቻ ቃል ።

ተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ በአጭርዋ ሕይወታዊ ዘመናቸው የፈጸሙዋቸው ታሪካዊ የሆኑ ደጋግ ሥራዎች በሕይወት ካሉበት ጊዜ ይልቅ በሞታቸው ገነውና ደምቀው ቀድመዋቸው ስለሄዱ ፤ እነሆ በጐ ሥራ መሥራት እንደምን ያለ ክብር እንደሚያወርስ ምስክር ሆኑ ።



የመጀመሪያዎቹ ፡ የጦር ቦይስካውቶች ስለ ተወዳጁ መስፍን 30 ኛ ቀን መታሰቢያ ያዘጋጁትን ድርሰት ለግርማዊነታቸው ሲያበረክቱ ።

ደጋግ ሰዎች ወደዚህ ዓለም ፈጥሮ ለላካቸው ለእግዚአብሔር ቅርብ ቤተ ሰብ ስለሆኑ ፤ በዚህ ዓለም ተድላ ደስታ እያደረጉ ከሚኖሩ ያልፋል ይጠፋል የማ

ይባለውን መንግሥተ ሰማያትን ወርሰው የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ ሆነው እንዲኖሩ ቆሎ ይጠራሉ ።




የመጀመሪያዎቹ የጦር ቦይስካውቶች በሠላሳኛው ቀን በልዑልነታቸው አስከሬን የአበባ አክሊል ሲያኖሩ።

ልዑል መኰንን መስፍን ሐረር በሕይወታቸው ሳሉ ይህን ዓለም አላፊና ቀሪ መሆኑን ተገንዝበው ሰው በዚህ ዓለም ሲኖር ጥሎት የሚሔደው መል ካም ሥራ ብቻ እንደሆነ ጥልቅ በሆነ ጠጣት ዕድሜያቸው መርምረው ደርሰውበታል።

ይኸውም ይታወቅ ዘንድ በዚህ ዓለም ለመኖር ዕድሜ ከሚያበድራቸው በማያልፈውና በማይጠፋው በጐ ሥራ ለሠሩና ለሚሠሩ የተዘጋጀውን ዘለዓለ ማዊ ቤት ለመውረስ በየጊዜው የሠሩዋቸው ደጋግ የትሩፋት ሥራዎች ቀድ መው በሞት አስጠሩዋቸው ።

## ወጣቱ መስፍን ልዑል መኰንን ሆይ !

ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየኸን ጀምሮ ምን ጊዜም ቢሆን በመንፈስ ከአንተ ጋር አልተለያየንም ፤ ደጋግ ሥራዎችህ በውነቱ ውድ የሆነውን መልክም ሰውነትህን በማንም ዘንድ አላስረሱም ። በአንተ ላይ ከፍ ያለ ተስፋ



የመጀመሪያዎቹ ፤ የጦር ፤ በይስከውቶች ፤ ያበባውን ፤ አክሊል ፤ በልዑልነታቸው ፤ አስከሬን ፤ ላይ ካስቀመጡ ፤ በኋላ ፤ የአብሮ ፤ አደግ ፤ ሰላምታቸውን ፤ ሰጥተው ፤ ሲሰናበቱ ።

የነበራቸው ሁሉ አንተን ከእጡ ጀምሮ ተስፋ ስለቆረጡ የዚህን ዓለም ኑሮ አስጠልቶዋቸዋል ። ልዑላን ልጆችህን እንደምን ጨቅነህ ጥለኻቸው እንደሄድክ በሰብን ጊዜ መሪር ኀዘናችን እየታደሰ ሔደ ፤ ግርማዊ አባትህና ግርማዊት እናትህ ዓይንህን አይተው ሳይጠግቡህ በሞት ስለቀደምካቸው ለተሰማቸው ኀዘን አማርኛ ሊገኝለት ከቶ አልተቻለም ።

በአጭርዋ የሕይወት ዘመንህ ሕፃናትን ፤ ሽማግሌውን ፤ አሮጊቱን ፤ ወጣቱን ፤ እንደየግብሩ ምን ጊዜ ሁሉን አስደስተህ ፤ ልቡን በኃዘን ጦር ወጋኸው ።


ከአቤል ጀምሮ በሰው ልጅ የደረሰና ለሰውም የተፈጥሮ ግዴታ የሆነው ሞት በአንተ ላይ ሲደርስ እንግዳ ሆኖ ታየ ። ሞት እንግዳ ሆኖ የታየው የአንበሳ ግልገል የነበርከው ወጣት መስፍን ያለጊዜው በድንገተኛ ሞት ስለሞትክ ነው ።



የመጀመሪያዎቹ ፡ የጦር ፡ ቦይስካውቶች ፡ በኅብረት ፡ የዘጋጁትን ፤ ድርሰት ፡ ለግርማዊነታቸው ፡ ባበረከቱ ፡ ጊዜ ፡ ግርማዊነታቸው፡ ጥልቅ ፡ በሆነ ፡ የኃዘን ፡ ስሜት ሲቀበልዋቸው ።

ኻያ አራት ሰዓት ባልሞላ ጊዜ የሚወዱህና የምትወዳቸው ግርማዊ አባትህና ግርማዊት እናትህ ከአጠገብህ ቢለዩህ ዓይናቸውን ለማየት ናፍቀህ ስትገሰግስ ምን ዓይነት አጋጣሚ አግኝቶ ዓይናቸውንና ዓይንህን ሳያዩ ፤ የከፋህንና


የተሰማህን ቅሬታ ሳይጠይቁህና አንድ ቃል ሳትመልስላቸው እንደ አጥቢያ ኰከብ የሚያበራው ዓይንህ በሞት እንቅልፍ ተዋጠ ።



በተወዳጁ መስፍን መኖሪያ ቤት ለ30 ኛው ቀን መታሰቢያ የተዘጋጀውን ድርሰት ለልዕልት ሣራ ሲያበረክቱ ልዕልትነታቸውም በድርሰቱ ላይ ያለውን የልዑልነታቸውን ፎቶ ግራፍ ጥልቅ በሆነ የኃዘን ስሜት ሲመለከቱ ።


ጣዕምና ለዛ የነበረው አንደበትህ በሞት ሰንሰለት ታሰረ ፤ ከሞትህ ቀን ጀምሮ በብዙ ሰዎች አንደበት በልዩ ልዩ ቋንቋ የተንቆረቆረውን ድርሰትና

መዝሙር ፤ እባክህ ጌታችን ቀና ብለህ አድምጥ የመጀመሪያዎቹ የጦር በይስ ካውቶች አሽከሮችህ ይህችን ድርሰት በስምህ እያበረከቱ ።



የመጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውቶች በልዑልነታቸው አስክሬን ላይ ያበባ አክሊል አስቀምጠው ሲመለሱ ።

መስከረም ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፮ ዓ ም በለመለመውና በለጋው ሰውነትህ እኛን መስለህ ከኛ ጋር የገባኸውን ቃል ኪዳን እያስታወስን ፤ አንተ በሥጋ ብትለየን እኛም ተራችን



ስለተወዳጁ መስፍን ሰላማኛ ቀን የተዘጋጀውን ድርሰት ለልዕልት ማራግዛው ለማበርከት በመኖሪያ ቤታቸው የጦር ባይስካውቶች ሔደው ካበረከቱ በኋላ ከልዕልትነታቸው ጋር የተነሡት ፎቶግራፍ ።

ደርሶ እስከንከተልህ በመንፈስ ከአንተ ጋር ሳንለይ እንድምንኖር እናረጋግጥልኻለን

# የመልካም ሰው ትውልድ ዘሩ እንደ

## ዋርካ ፍሬ የበዛ ነው ።

ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ ጀምሮ ትውልድ ሲያልፍ ትውልድ ሲተካ ከዚህ ደርሰዋል ። ልዑል መኰንን መስፍን ሐረር ምንም በወጣትነት ዕድሜያቸው ከዚህ ዓለም በሞት ቢለዩ ከአብራካቸው የተከፈሉ ልዑላን ልጆቻቸውን አፍርተው ልን ስላለፉ ዓይናቸውን በዓይናቸው ለማየት ችለናል ።

ሰው በዚህ ዓለም ሲኖር የልጅ አበባ ለማየት በኀይል የሚጣጣረው ፣ ሕይወታዊ ኑሮውን በደስታ ለማስጌጥና ከዚህ ዓለም ካለፈ በኋላ ስሙና ታሪኩ እንዳይጠፋ ነው ። ለምሳሌ አንድ ሰው በምድራዊ ኑሮው የሀብት ጌታ ሆኖ ልጅ ከሌለው ሀብቱን እንዳለ አድርጎ አይቆጥረውም ዕለተ ሞቱ በደረሰም ጊዜ ንብረቱን የሚያወርሰው ለቤተ እግዚአብሔርና ወይም በተለይ ለሚወደው ነው ።

ልጅ ያለው ሰው ግን ከዚህ ዓለም ቢያልፍ በአካላዊ ሥጋ በግዙፍ መታየቱ ቀረ እንጂ ፣ ከአካሉ ተከፍሎ የወጣው ዘሩ ከሰውነቱ ቅርጽ የሚበልጠውን ክፍል ይዞ የሚወለድ ስለሆነ ፣ በሚያየውና በሚያውቀው ሁሉ እንዳለ ሆኖ ሲወሳ ይኖራል ።

ልዑል መኰንን ተወዳጅና ተናፋቂ ግብራቸውን ይዘው በወጣታዊ ዕድሜያቸው ከዚህ ዓለም በመለየታቸው ፣ በወላጆቻቸውና በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ የማይረሳ መራራ ኀዘን ቢተክሉም ፣ አበርክተውን የሔዱትን ልዑላን ልጆቻቸውን ስንመለከት ፣ ኃዘናችንን መርሳት አለብን ።

ተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን መስፍነ ሐረር በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የጦር በይስካውት ትምህርት ቤት የበላይ ጠባቂና መሪ ሆነው ከፈጸሙት መልካም ተግባር በላይ ፣ በዚያን ጊዜ በትምህርት ቤቱ የነበሩት ተማሪዎች በማህበራዊ ኑሮ በአንድ የሕብረት መንፈስ ተሳስረው እንዲኖሩ የነበራቸው ከፍ ያለ መልካም ፈቃድና ጥረት ቀደም ብሎ ተገልጿል ።

የመጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውቶች በልዑልነታቸው በጐ ሥራና ሰብአዊ ርኅራኄ ልባቸው የተነካ ስለሆነ ፣ ኀዘናቸውን ለማስታገስ ለሰላሣኛው ቀን የአበባ አክሊል በአስከሬናቸው ላይ ለመታሰቢያ አስቀምጠው ከግርማዊነታቸው ጋር ሲገናኙ ስለናንተ የነበረውን አሳብና የጀመረውንም ታውቃላችሁ ። ርሱ በሞት ቀድሞ ቢሔድ የጀመረው ሁሉ ከፍጻሜ እንዲደርስ እንረዳችኋለን ሲል ልባዊ በሆነ የኀዘን ስሜት ግርማዊነታቸው ተናግሮ ነበር ።

እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በፍቅር መንፈስ ትባብሮ ራሱንና አገሩን እንዲረዳ የተቀደሰ ፈቃድ ያለው ግርማዊነታቸው በልዑል መኰንን መስፍነ ሐረር

የተጀመረው የመጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውቶች ጉዳይ ፤ ከፍጻሜ እዲደርስ መልካም ፈቃድ እንዳላቸው ገለጹ ።

የመጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውቶች በየጊዜው ስብሰባ እያደረጉ ጉዳዩን ካጠኑ በኋላ ፤ ከልዑልነታቸው አንዱ አካል ልዑል ወሰን ሰገድ መኰንን የመጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውቶች ማኅበር የክብር ፕሬዚዴንና መሪ እንዲሆኑ ለግርማዊነታቸው አመለከቱ ።

ለመልካም ሥራ ቀናዒ ያላቸው ፤ ልጆቻቸውንም ከኢትዮጵያ ልጆች በብልጫ የማያዩ ግርማዊነታቸው ፤ ይህን ጥያቄ በደስታ ተቀብለው የማህበሩ የክብር ፕሬዚዳንና መሪ እንዲሆኑ ስለፈቀዱ ፤ እነሆ ልዑልነታቸው የመጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውቶች ማኅበር የክብር ፕሬዚዳንና መሪ ሆኑ ።

በዚሁም ጊዜ ከመጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውቶች ቀጥሎ የተመለከተው ንግግር ተደረገ ።

## ልዑል ሆይ ።

በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የጦር በይስካውት በ፲፱፻፳፯ ዓ ም በተቋቋመ ጊዜ ዕድል አግኝተን በትምህርት ቤት የነበርን የእስካውት ተማሪዎች እነሆ በልዑልነትዎ ፊት ተሰብስበናል ።

ዛሬ በዚህ የምንገኘው በአዲስ አበባና በዙሪያው ያለነው ብቻ እንጂ በሥራ ምክንያት በየጠቅላይ ግዛቱ የሚኖሩት ለጊዜው አልተገኙም ።

የግርማዊነታቸው መልካም ፈቃድ ሆኖ ከላይ የገለጽነው ትምህርት ቤት በተመረቀበት ቀን ልባዊ በሆነ በኃዘን ስሜት የምናስታውሳቸው ፤ ልዑል አባትዎ በ፲፩ ዓመት ዕድሜያቸው በችግራችን ሁሉ እንዲረዱን በበላይ ጠባቂነት ተሰጡን ።

ሞት ሥጋ ለለበሰ ፍጡር ሁሉ የግድ ዕዳ ሆኖ ልዑል አባትዎ ቀድመውን ቢሄዱም ከአብራካቸው የተከፈሉ ልዑላን ልጆቻቸውን አበርክተውን ስለሄዱ ፤ በሕይወት እንዳሉ እንቆጥረዋለን ።

የመጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውቶች በልዑልነታቸው ጠባቂነትና መሪነት ስንተዳደር ልዑልነታቸው የጣሉብን ደጋግ ሥራዎች ምንጊዜም ከቶ አይረሳንም ።

በልዑልነታቸው የበላይ ጠባቂነትና መሪነት እንተዳደር የነበርን ታዛዥዎችዎ ፤ ልዑልነታቸው ምንም ከዚህ ዓለም በሞት ቢለዩን ልዑልነትዎን የመሰለ አካላቸውን ስለተካልን በተወዳጁ አባትዎ ምትክ ልዑልነትዎ ጠባቂናመሪ እንዲሆነን ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አመለከትን ።

ግርማዊነታቸውም ወሰን በሌለው ቸርነቱ ጥያቂያችንን ስለተቀበለን ፤ ልዑልነትዎ ከታዛዦቹ ጋር ፎቶግራፍ ለመነሣት በመካከላችን በመገኘቱ ልባችን በደስታ ተነክቷል ።

## ልዑል ሆይ

ተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን በመጀመሪያው የጦር በይስካውት ትምህርት ቤት በበላይ ጠባቂነታቸውና መሪነታቸው ያስገኙትን የሥራ ፍሬ በአጭር የሚገልጽ መጽሐፍ በሀብረት አዘጋጅተን በማሳተም ላይ ስለሆን ፤ የሚፈለገው ዝርዝር ሁኔታ በመጽሐፉ ላይ ስለሚገኝ ፤ አሁን ማተት አስፈላጊ መስሎ ስላልታየን አልፈነዋል ።

ከመልካም ሰው የተገኘ የዘር ፍሬ በዛላው ይታወቃል ።

ልዑልነትዎ መሪያችንና የማህበራችን የክብር ፕሬዚዳን በመሆኑ ከፍተኛ ዕድል አግኝተን ሕይወታችንን እንደ አዲስ ልደት ቆጥረነዋል ።

ዕድሜ ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
" ለግርማዊት እቴጌ
" ለንጉሣውያን ቤተ ሰብ
ኢትዮጵያ በነፃነቷ ለዘለዓለም ትኑር
የመጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውቶች ነሐሴ ፳፯ ቀን ፲፱፻፵፱ ዓ ም

ንግግሩ እንዳለቀ ልዑል ወሰን ሰገድ መኰንን የሚከተለውን አጭር መልስ ተናገሩ ።

«ስለ አባቴ ኅዘንና ስለኔም ላሰባችሁት ከልቤ አመሰግናችኋለሁ ። በአባቴ የተጀመረውና የታሰበው ከፍጻሜ ደርሶ ማኅበሩ እንዲስፋፋ ተስፋ አደርጋለሁ» ።

የልዑልነታቸው ንግግር እንደ ተፈጸመ ከመጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውቶች ጋር ልዑልነታቸው ፎቶግራፍ ተነሥተው በመጡበት አኳኋን ወደ ቤተ መንግሥት ተመለሱ ።


ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ ተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን ለመጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውቶች የበላይ ጠባቂና መሪ እንዲሆኑ የሰጥዋቸው በአሥራ አንድ ዓመት ዕድሜያቸው ነበር ።

የልዑልነታቸው ልጅ ልዑል ወሰን ሰገድ መኰንን በአሥራ አንድ ዓመት ዕድሜያቸው በአባታቸው ምትክ የማኅበራቸው የክብር ፕሬዚዳንና መሪ መሆናቸው ነው ።

# የማይረሳ ታላቅ ውለታ ፡፡

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ አባት እንደ መሆናቸው መጠን ፤ ከአብራካቸው የተከፈሉ ልጆቻቸው ከያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ጋር ቤተ ሰብ እንዲሆኑ በየጊዜው የሚፈጽሙትና የፈጸሙት ታላላቅ ሥራ በማንም ልቦና ሳይዘነጋ ይኖራል ። ነቢዩ ዳዊት ፤ «ልጆችህ እንደ ወይራ መንትዮች በማዕድህ ዙሪያ ይሆናሉ ። የልጅ ልጅህንም ታያለህ ፤ እነሆ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው እንደዚህ ይባረካል» ያለው ትንቢታዊ ቃል ከመልካም አድራጎታቸው ጋር የተያያዘ ሆኖ ስለተፈጸመ ደስ ይለናል ።

የመጀመሪያዎቹ የጦር ቦይስካውቶች የበላይ ጠባቂያቸውና መሪ ያቸው ልዑል መኰንን በሞት ከዚህ ዓለም ቀድመው ቢለዩዋቸው በልዑል ነታቸው ተጀምሮ የነበረው ማናቸውም ጉዳይ እንዲከናወን አስፈላጊውን ከማ ድረጋቸውም በላይ ፤ የልዑልነታቸውን የመጀመሪያ ልጅ ልዑል ወሰን ሰገድ መኰንን በአሥራ አንድ ዓመት ዕድሜያቸው ለማኅበራቸው የክብር ፕሬዚዳ ንና ጠባቂ እንዲሆኑ መፍቀዳቸውን ሲያስቡት እንኳን በራሳቸው በትውልዳ ቸው ውለታውና መታሰቢያው ሳይረሳ ይኖራል ።



ልዑል ወሰን ሰገድ መኰንን ከመጀመሪያዎቹ የጦር ቦይስካውቶች ጋር ።

# የቦይስካውቶች ማህበራዊ ድርጅት

የመጀመሪያዎቹ የጦር ቦይስካውቶች ማህበር ዓላማውንና ድርጅቱን በው ስጥ ደንቡ አስፋፍቶ ወደፊት ይገልጻል ።

ማህበሩም ከሚሠራቸው አውራ ከሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያውን ምዕራፍ የሚይዘው የልዑል መኰንን መስፍን ሐረር መታሰቢያ ነው ።

ወደፊት የሚስፋፋውን ሥራ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት የቦይስካውት ድርጅት ክፍሎች ግንኙነት እያደረጉ አስፈላጊውን በመተባበር ይፈጽማሉ ።

፩ኛ| የመጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውቶች
፪ኛ| የክብር ዘበኛ ወጣት በይስካውቶች
፫ኛ| የፖሊስ ሠራዊት ወጣት
፬ኛ| የትምህርትና የሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ሰላማዊ በይስካውቶች ናቸው።

የአራቱ ማህበራዊ በይስካውቶች አባሎች ስብሰባ እያደረጉ የድርጅቱን አፈጻጸም ያከናውናሉ ።

የልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ የእስካውት በዓል ተብሎ ወደፊት በየ ዓመቱ በሚከበርበት ቀን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መል ካም ፈቃዳቸው ሆኖ በሚገኙበት አራቱ ማህበራዊ ክፍሎች ልዩ ልዩ ትዕ ይንት እያሳዩ በፈጸሙት ተግባር ብልጫ ላላቸው በይስካውቶች በግርማዊነታ ቸው ሽልማት ይሰጣል ።

ተፈጸመ ።

---

ስለ መሪያችንና ጌታችን ልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ መስፍነ ሐረር የአርባኛው ቀን መታሰቢያ ከመጀመሪያዎቹ የጦር በይስካውቶች ተዘጋጅቶ የነበረ የኀዘን መግለጫ ።

በአሥራ ዘጠኝ መቶ በኻያ ስድስት
በዘመነ ተድላው በዓመተ ምሕረት
ለኢትዮጵያ ወጣቶች ሊሰጠን ትምህርት
ሥልጣኔና ዕውቀት ሊገበይበት
ተዘጋጅቶ ሕግን ባማረ ውበት
በወርቃ መስከረም ጠቅል መርቆት
ተሰጠ ለእስካውቶች እንዲማሩበት ።
ለዓላማው ጥበቃ ስላሻ መኰንን
ተመርጦ ተሰጠን የሐረሩ መስፍን ፤
እሱም ለጥበቃው ሲቀበል አደራ
እብሮ ተረከበ የእስካውትን ባንዲራ
በዚህም መሠረት ሠርቶና እያሠራ
የእስካውትን ሠራዊት በደንቡ እየመራ
ትንሽ ትልቅ ሳይል ሆኖ ባልንጀራ
ያስተዳድር ነበር ከመምህራን ጋራ ።
አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በየበዓላቱ
ፍራፍሬ ብስኩት ሳይቀር በያይነቱ

እሲዞ በአሽከሮች አምጥቶ ከቤቱ
ያድለን ነበረ መኰንን ወጣቱ ፤
ይልቁንም ደግሞ ደጉ ጌታችን
ሁል ጊዜ ሳይለይ ከመኻላችን
በክርስቲያን በዓል በፋሲካችን
ያበላን ነበረ ሥጋ ፍትፍቱን ።
በዚህ አያያዙ እስካውትን ሲመራ
ትምህርትን ሲያስፋፋ እውቀትን ሲያበራ
እስካውቶችም ደግሞ በቃል ኪዳናቸው
አጥንታቸው ደቆ ፈሷል ደማቸው ።

ከዚያም ባርበኝነት ብዙ እየታገሉ
በኢትዮጵያ ተራሮች በዱር በገደሉ
የወደቁ ጀግኖች ብዙ እስካውቶች አሉ

በእግዚአብሔር እርዳታ ባባጠቅል ብርታት
አልፎ ሥቃይ ጭንቁ የመከራው ሰዓት
መሪያችንም መጥቶ ከተሰደደበት
መበታተን ቀርቶ አግኝተን ነፃነት
እንኖር ነበረ በጣም በመደሰት ፤

እንኳን ለአሽከሮቹ ለኛ እስካውቶች ቀርቶ
ለሕዝብ ያስብ ነበር ሌትና ቀን ተግቶ
ካለንበት ክፍል አሰብስቦ ጠርቶ
እርስት ሊያሰጠን ሙሉ ተስፋ ሰጥቶ
አይዟችሁም ሲለን ከልብ አበራቶ
ጥሎን ሄደ ከሜዳ ላይ ትቶ ።

በእስካውት ሞያ እንዲያ ሲያምርብህ
በጀኔራልነት ይምጣ ዩኒ ፎርምህ
በፖይሎንትነትም አንድ እንከን የሌለህ
የብዙ ቤተሰብ የልጅ አባት ነህ
ልጆችህ እስኪያድጉ እኛ እስክንደረጅ
ሀገር ጥሎ መሄድ ለምንም አይበጅ
የልዑላን አባት ያባ ጠቅል ልጅ
የድሆች አሳቢ የልጅ አማላጅ
የድሆች ፋሲካ የጮማ የጠጅ
እንዴት ሜዳ መቅረት መኰንን ከደጅ
ገብተህ ከመንበርህ ተገኝልን እንጅ ።
የሐረሩ መስፍን የእስካውቱ መሪያችን
አንተ አልነበርክም ወይ ለኛ ምሰሶአችን
ጣሪያና ግድግዳው ማገር ሰብሳቢያችን
ሞትን እንዴት መረጥክ መሪር እሬቱን ።
የጥንት አሽከሮችህ እስካውቶች በሙሉ
በውጭም በግቢ በያገሩ ያሉ
ጠመንጃ በማንሳት ፕሬዛንቴ እያሉ
ለመልክም ምግባርህ ለርኅራኄህ ሁሉ

---

የእስካውት ጦር መሪ የመጀመሪያው
ወጣቱ መኰንን ተፈሪ ጋሻው
ያሁኑም እስካውቶች ጥበቡን ወደው
ያቀደውን ፕላን ሳይጨርስ ምነው ።

የጀግኖች ዓላማ መኰንን ተፈሪ
የሐረሩ መስፍን ሥርዓት አስከባሪ
ተኳሹ ወታደር ጥበብ አሳማሪ
ቀረው እንደ ዋዛ ያገር ተቆርቋሪ።
በግንቦት ፬ ቀን በዕለተ ሰንበት
አቶቹ ናፍቀውት ገባላቸው ገነት
ብርሃናችን ጠፍቶ ተለየን ድንገት
መላእክት ሰማይ አቅፈው ወሰዱት
የድሆች እንጀራ ያገር መድኃኒት
ተጨንቅን ተጠበብን በመኰንን ሞት ።
በዚያ በነበልባል በእሳት ገሞራ
በአምስቱ ዘመናት በሥቃይ መከራ
አውሮፓ ተሻግሮ ላገር የሚሠራ
በግርማው መኰንን ጠላት የሚያስፈራ
ካርበኞች ተባብሮ ከተፈሪ ጋራ
ድል አድራጊው ጀግና ሕዝቡን የሚያኰራ ።
ኢትዮጵያ ደስ ብሏት ነፃነት አግኝታ
ሕዝቡም ተሻሽሎ በኑሮ ደስታ
እኛም ብለን ነበር መሪው የኛ ጌታ
ምን ጊዜ ፈጠነ ልዑል በሹልክታ ።
ሲሆን በሰማኒያ በመቶ ነበር
እንዴት በሰላሣ ይያዛል ምድር
ፀሐይ ወጣ ብላ ታየችው በቀትር
ተከትሏት ሄደ ከሷ ጋር ሊኖር ።
እንዲህ ያለ ጀግና እንዲህ ያለ ብርቱ
ዋ ቀረ ዋ ቀረ ዋ ቀረ በከንቱ
ዓይኖቹም እጆቹም ዛለ ሰውነቱ
አዘነ ተከዘ መላው በየቤቱ ።
መኰንን ተፈሪ መልካሙ ገበሬ
ዘሩን ዘርቶልናል ሊሆኑልን ፍሬ
ይኸው አየናቸው ብቅ ብለው ዛሬ ።
እሱ ባይወለድ ዳግም መኰንን
አይገኙም ነበር ወጣቶች ልዑላን
እነሱም ከሣራ ከዳዊት ወገን
ብሩክ እንደ አባቱ ታጣቂው መስፍን

መለከት ሲነፋ ነጋሪት ሲመታ
ነዓ ኅቤየ ብሎ ይቀበልህ ጌታ ።
ግርማዊ አባ ጠቅል ኀዘኑ ይብቃዎ
ግርማዊት እቴጌ ኀዘኑ ይብቃዎ
ኀዘን የሚያስረሱ ተክቷል ልጅዎ ።
ልዕልት ሣራ ሚዜው ኀዘኑን ይሰልቹ
አልሞተም መኰንን አሉ ወጣቶቹ ።
እህት ወንድሞቹም ልዑላት ልዑላን
ዛሬ በቃ በሉ ተውት ኀዘኑን ።

አዳም በበደል የፈጠረው ክሶ
ሞትን በሞት ሽሮ አዳነው መልሶ ።
ፍጡር ቢተባበር እጅግም ቢዋደድ
የሚወደው ልጁ ይለየዋል በግድ ።
እንኳን የወለደው ያወቀው አዘነ
እምቢ ብሎ ሔደ ወጣቱ መኰነ ።
የኛ ወጣት መስፍን ሔደ ተሰደደ
ምንም አልተገኘ እየራቀ ሔደ ።
ዓይናማው መኰንን የኛ መልከም ጌታ
ያንን ለዛ ይዞ በማጥን ተመታ
በድለንህ እንደሁ አርግልን ይቅርታ ።
ከግርማዊ አባቱ ተለየ መኰንን
አቃጥልዋቸው ሔደ በመረረ ኀዘን ።
መለስ በል መኰንን አታምርር በውነት
ናፍቀናል ጓጉተናል ዓይንህን ማየት
ማንም ሰው አልቻለ አንተን ለመርሳት
ጀግናው ልጅ መኰንን እንዴት ትረሳለህ
በሁሉም ጦር ሜዳ ተሰልፈህ አብረህ
በስደትም ሆነ ከቶም አልተለየህ
እጅግ ጠቅመህ ነበር ባጭርዋ ሕይወትህ
ምነው አሁን ጨከንክ በጣም አምረርህ
ከግርማዊ አባትህ ተለይተህ ሔድህ

አባትም እናትም በጣም ይራራሉ
ከልጃችን ቀድመን እንሒድ ይላሉ ።
ነገር ግን አይሆንም አይደረግም
ከአዳም ቀድሞ ሔድዋል በሞት አቤልም ።
ልጅ ግን ይጨክናል አይራራም እንዳባት
ድንገት ብድግ ብሎ ይሔዳል በፍጥነት ።

እጅግ ተሳቀቁ ልዑላን ልጆችህ
ጥዋት ወጣ ብለህ በዚያው በመቅረትህ ።
በጦር ሜዳም ሆነ ደግሞም በስደት
ሣትለይ ኖረሃል ምን ጊዜም ሰዓት ።
አሁን ግን ተለየህ ከአባት ከናትህ
በግንቦት አራት ቀን ጨክኘ አገኘህ ።
በጥቅምት ፳ ቀን በዕለተ ሠሉስ
ተወልደህ ነበረ ከተባረከ ጽንስ ።
በግንቦት ፬ ቀን በዕለተ እሁድ
ወደአባት እናትህ በግስገሣ ስትሔድ ።
ማነው የጠበቀህ በመካከል መንገድ
ከሁሉም ለይቶ የወሰደህ በግድ ።
እጅግ ደግነትህ መልካሙ ሥራህ
ይጠብቅህ ነበር በፊትህ ቀድሞህ
ዋጋህን ለመክፈል ድንገት አስጠራህ ።
በዚህ ዓለምና በማያልፈው ዓለም
ስምህም ይጠራል ዓለም ዘለዓለም ።
እንግዲህስ ይብቃ ሁሉም ሰው ይጽናና
መስፍኑ አይረሳም በሁሉም ሕሊና ።

የመጀመሪያዎቹ የጦር ባይ ለጊዜው ስማቸው የተገኘው ስካውት ተማሪዎች የነበሩት ቀጥሎ በሬደልተራ ተጽፍዋል።

(1) ልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ መስፍነ ሐረር ።

| ተ ቁ | ስምና ያባት ስም ። | | ማዕረግ |
|---|---|---|---|
| 2 | ኃይለ ሚካኤል | ገብሬ | የመ፡ አለቃ |
| 3 | ሀብቷሙ | ዘርጋው | አቶ |
| 4 | ኃይሌ | ተክሌ | " |
| 5 | ኃይሌ | ወ ጊዮርጊስ | » |
| 6 | ኃይሉ | በላቸው | » |
| 7 | ኃይሉ | ቀንዓ | ሻለቃ |
| 8 | ኃይሉ | ስብሐት | አቶ |
| 9 | ላቀው | ይፍሩ | » |
| 10 | ለማ | ወርቁ | " |
| 11 | ለማ | አመጠ | » |
| 12 | ልዑል ሰገድ | ዘወልዴ | " |
| 13 | ለገሠ | ገብረ ሚካኤል | .. |
| 14 | ለማ | ብሩ | " |
| 15 | ለማ | አጅብቸው | " |
| 16 | ለገሠ | ወልደ ሐና | የ፻ አ |
| 17 | ለገሠ | ወልደ ገብርኤል | አቶ |
| 18 | ለማ | ወ ሰማያት | አቶ |
| 19 | ምሕረት | ገብረ ሰላም | ሻለቃ |
| 20 | መሸሻ | ገብሩ | ሻምበል |
| 21 | መኰንን | ደንባው | " |
| 22 | ማሩ | ጋተው | " |
| 23 | መርሻ | ይርጉ | " |

| ተራ ቁ | ስምና | የባት ስም | ማዕረግ |
|---|---|---|---|
| 24 | መኰንን | ነጋ | አቶ |
| 25 | መኰንን | ወልዴ | ,, |
| 26 | ሙሉጌታ | አየለ | ,, |
| 27 | ማንያዘዋል | ሀ/ ሚካኤል | ,, |
| 28 | መኰንን | ዘውዴ | ,, |
| 29 | መንግሥቱ | ገብሬ | ,, |
| 30 | ሙሉጌታ | እምሩ | ,, |
| 31 | ሞገስ | አየለ | ,, |
| 32 | ምትኩ | ኪዳነ ማርያም | ,, |
| 33 | መብራቱ | አቻሚለህ | ,, |
| 34 | ሞገሴ | ሀብተየስ | ,, |
| 35 | ሙላቱ | ወልደ ጻድቅ | ,, |
| 36 | መለሰ | ጀንበሬ | ,, |
| 37 | ምትኩ | ወሰና | » |
| 38 | መኰንን | ከበደ | » |
| 39 | መኰንን | ማንደፍሮ | » |
| 40 | ማሞ | ሀብተ ሥላሴ | ,, |
| 41 | ሙሉጌታ | አየለ | » |
| 42 | መርሻ | ተክለ ሥላሴ | » |
| 43 | ማንደፍሮ | | » |
| 44 | መኰንን | ደስታ | » |
| 45 | ማሞ | ሀብተ ማርያም | » |
| 46 | ማህሌ | ዕንቈ ሥላሴ | የመ/ አ |
| 47 | ሥዩም | መንገሻ | |
| 48 | ሥምረተ አብ | ገብረየስ | |
| 49 | ሰይፉ | ወልደ ኪሮስ | |
| 50 | ሥዩም | መኰንን | |
| 51 | ሥን | ገብረ ሕይወት | |
| 52 | ሥዩም | ዘለቀ | |
| 53 | ሥዩም | ወ/ ማርያም | |
| 54 | ሰይፉ | ወ/ ጻድቅ | |
| 55 | ሺፈራው | ፀጋ | |
| 56 | ሽፈራው | ወ/ ማርያም | |

| ተራ ቍ | ስምና ያባት ስም ። | ማዕረግ |
|---|---|---|
| 57 | ሺፈራው ኪዳኔ | |
| 58 | ሺፈራው ገ መድኅን | |
| 59 | ሺፈራው ገ ማርያም | |
| 60 | ሺፈራው ገ ጻድቅ | |
| 61 | ብርሃነ መስቀል | ደጃዝማች |
| 62 | ቃኘ ዓለሙ ወ ሥላሴ (ክቡር) | ሻምበል |
| 63 | ብርሃነ ሥላሴ ሣህሌ | ” |
| 64 | በጋለ መንገሻ | የመ አ |
| 65 | በትረ ሥላሴ ተስፋ | ” |
| 65 | በቀለ ወ ሥላሴ | |
| 66 | በቀለ ወ/ ኪዳን ። | |
| 67 | በቀለ ወዳጆነህ ። | |
| 68 | በቀለ ካሣ ። | |
| 69 | በላቸው ገዝሙ ። | |
| 70 | በጋለ ተሰማ ። | |
| 71 | ብርሃኑ አበሩ ። | |
| 72 | በላይነህ ዘለቀ ። | |
| 73 | በቀለ ሰይፋ ። | |
| 74 | በቀለ ገብሬ ። | |
| 75 | ብጡል ገሠሠ ። | |
| 76 | በቀለ እሸቴ ። | |
| 77 | በለጠ ወ መድኅን ። | |
| 78 | በየነ ደስታ ። | |
| 79 | በቀለ ኃ ገብርኤል ። | |
| 80 | በቀለ ወንድሙ ። | |
| 81 | በቀለ ተ ሃይማኖት ። | |
| 82 | በልሁ ኃ ማርያም ። | |
| 83 | ብሥራት ኃ ገብርኤል ። | |
| 84 | በቀለ ስብሐት ። | |
| 85 | በላቸው ገ ጻድቅ ። | |
| 86 | በቀለ እስጢፋኖስ ። | |
| 87 | በቀለ መኰንን ። | |

| ተ ቍ | ስምና ያባት ስም ። | | ማዕረግ |
|---|---|---|---|
| 88 | በቀለ | አስማረ ። | አቶ |
| 89 | ታምራት | ዘገየ ። | ሌ/ኰሎኔል |
| 90 | ተፈሪ | ዘውዴ ። | አቶ |
| 91 | ታደሰ | ሸዋ ሰገድ ። | ሻምበል |
| 92 | ተገኝ | ገ/ ማርያም ። | የመቶ አ. |
| 93 | ታደሰ | ማርያም ። | አቶ |
| 94 | ተክለ ማርያም | ካሣ ። | |
| 95 | ታደሰ | አይተንፍሱ ። | |
| 96 | ታደሰ | ወ/ መስቀል ። | |
| 97 | ተክሉ | ጕበዘ ። | |
| 98 | ታምራት | አለኝታ ። | |
| 99 | ተስፋዬ | ጣሰው ። | |
| 100 | ቱፋ | ጐሹ ። | |
| 101 | ተስፋ | ተክሉ ። | |
| 102 | ተሠራ | ዘለቀ ። | |
| 103 | ተፈራ | ዘለቀ ። | |
| 104 | ተሾመ | ገብሩ ። | |
| 105 | ተፈራ | ዘለሌ ። | |
| 106 | ተስፋዬ | ወንድም አገኘሁ ። | |
| 107 | ተፈራ | መሸሻ ። | |
| 108 | ተሻለ | ደሬሣ ። | |
| 109 | ተድላ | ዓለሙ ። | |
| 110 | ተሾመ | በየነ ። | |
| 111 | ታደሰ | ከስሜ ። | |
| 112 | ተስፋዬ | መኩሪያ ። | |
| 113 | ታዬ | ካሣዬ ። | |
| 114 | ተሾመ | በየነ ። | |
| 115 | ቾሩ | ዘርፉ ። | |
| 116 | ታዬ | ሀ/ ማርያም ። | |
| 117 | ተሰማ | ወ/ ዮሐንስ ። | |
| 118 | ታደሰ | ሀ/ ሚካኤል ። | |

| ተራ ቁ· | ስምና ያባት ስም ። | | ማዕረግ |
|---|---|---|---|
| 119 | ተፈሪ | ያዘው ። | |
| 120 | ነዲ | በዳዳ ። | |
| 121 | ንጉሤ | አበራ ። | |
| 122 | ንዋይ | ባወቀው ። | |
| 123 | ነጋ | ተክሉ ። | |
| 124 | ንጋቱ | የሺነህ ። | |
| 125 | ነጋሽ | ሀ ወልድ ። | |
| 126 | ነጋሽ | ዘለቀ ። | |
| 127 | ነጋሽ | ገ መስቀል ። | |
| 128 | ንጉሤ | ድረሴ ። | |
| 129 | ዐቢይ | አበበ (ክቡር) | ብርጋዴር ጄኔራል |
| 130 | አባተ | አሊ | ሌ ኰሎኔል |
| 131 | አንበርብር | አበበ | ሻምበል |
| 132 | አሰፋ | መኰሪያ | " " |
| 133 | አስፋው | ወ/ ማርያም | የመቶ አለቃ |
| 134 | አበበ | ወ/ ጊዮርጊስ | " " |
| 135 | አስፋው | ፊጩርቆሴ | |
| 136 | ዓለማየሁ | ተፈራ | ሻለቃ |
| 137 | ዓለማየሁ | ጠይቃቸው | " " |
| 138 | አበበ | ጋሻው በዛ | ሻምበል |
| 139 | አበበ | ኪዳኔ | |
| 140 | አስፋው | ወ ጊዮርጊስ | የመቶ አለቃ |
| 141 | አሰፋ | ጣሰው | |
| 142 | አየለ | ወ ማርያም | |
| 143 | አልታዬ | ደምሴ | |
| 144 | አበበ | ዘውዴ | |
| 145 | ዓለማየሁ | ከልካይ | |
| 146 | አግደው | ሀብቴ | |
| 147 | አበሩ | ብርቄ | |
| 148 | አየለ | ተሰማ | |
| 149 | አዳል | ተሰማ | |
| 150 | አበበ | ዘለለው | |
| 151 | ዓለማየሁ | በላይነህ | |

| ተ ቊ | ስምና ያባት ስም ። | | ማዕረግ |
|---|---|---|---|
| 152 | አረጋ | ደምሴ | አቶ |
| 153 | አበራ | በዳኔ | |
| 154 | አበበ | ተበጀ | |
| 155 | አበበ | ግፋው ወሰን | |
| 156 | አበበ | ቱሉ | |
| 157 | ዓለማየሁ | አስፋው | |
| 158 | አዳል | በዛብህ | |
| 159 | አስፋው | ወ/ ጊዮርጊስ | |
| 160 | አስፋው | በቀለ | |
| 161 | አርጋው | ገብረ ጊዮርጊስ | |
| 162 | አለማየሁ | ኃይሌ | |
| 163 | አሸብር | ገብረ እግዚአብሔር | |
| 164 | አያሌው | ሙሉጌታ | |
| 165 | አምበሉ | መዝለቂያ | |
| 166 | አበበ | ዲማ | ም/ ያ/ አለቃ |
| 167 | አባተ | አሻሜ | |
| 168 | አዱኛ | ፌይሣ | |
| 169 | አበበ | ወርቁ | |
| 170 | አሰፋ | ሽበሺ | |
| 171 | አባተ | መንግሥቱ | |
| 172 | ዓለማየሁ | የለው ከልካይ | |
| 173 | አውላቸው | ሙሉጌታ | |
| 174 | አሻግሬ | ገብረየስ | |
| 175 | አየለ ማርያም | ጌታ | |
| 176 | አዲሴ | ዘውዴ | |
| 177 | አየለ | አስፋው | |
| 178 | አረጋ | ስብሐት | |
| 179 | እሸቴ | አበበ | |
| 180 | ዓለማየሁ | አርጋው | |
| 181 | አየለ | ተፈራ | |
| 182 | አበበ | ማኅተመ ወርቅ | |
| 183 | ከበደ | ይመር | የሻለቃ |
| 184 | ከበደ | ያዕቆብ | " " |

| ተ ቍ | ስምና ያባት ስም ። | | ማዕረግ |
|---|---|---|---|
| 185 | ክፍሌ | ደስታ | የሻምበል |
| 186 | ከበደ | ሀ ማርያም | ,, ,, |
| 187 | ከበደ | ወ ጊዮርጊስ | አቶ |
| 188 | ከበደ | ምትኬ | |
| 189 | ከበደ | ወ መስቀል | |
| 190 | ከበደ | ደስታ | |
| 191 | ከበደ | ቸርነት | |
| 192 | ከበደ | ገብሬ | |
| 193 | ከበደ | ወ ኪሮስ | |
| 194 | ከበደ | እሸቴ | |
| 195 | ከበደ | ታደሰ | |
| 196 | ከልክሌ | እርገጤ | |
| 197 | ከተማ | ወ ጊዮርጊስ | |
| 198 | ክፈተው | መኰንን | የ፲ አለቃ |
| 199 | ከበደ | ባልቻ | |
| 200 | ወሰን የለህ | ወ ኪሮስ | የሻለቃ |
| 201 | ወርቅ አለማሁ | ተክለ ሃይማኖት | የሻምበል |
| 202 | ወልደ አረጋይ | መምሬ | የመቶ አለቃ |
| 203 | ወንድሙ | ተሰማ | አቶ |
| 204 | ወንድሙ | ያደቴ | የ፶ አለቃ |
| 205 | ወንድሙ | በየነ | አቶ |
| 206 | ወላና | ኩሊ | |
| 207 | ውብሸት | ክፍሌ | |
| 208 | ውቤ | ስለሺ | |
| 209 | ወልደ ዳዊት | አባ ታቦር | |
| 210 | ወልደ አብ | ደጀኔ | |
| 211 | ወርቁ | ደስታ | |
| 212 | ወንድሙ | ወልደ ሩፋኤል | |
| 213 | ወንድም ሀብቴ | ደስታ | |
| 214 | ውብሸት | ዘወልዴ | |
| 215 | ወንድሙ | ወልደ ኪዳን | |

| ተራ ቍ | ስምና ያባት ስም | | ማዕረግ |
|---|---|---|---|
| 216 | ዘለለው | እንደሻው | የሻምበል |
| 217 | ዘውገ | በቀለ | የመቶ አለቃ |
| 218 | ዘውዱ | ዳመና | » » |
| 219 | ዘለቀ | ወልደየስ | አቶ |
| 220 | ዘኬዎስ | ገብረ እግዚአብሔር | » » |
| 221 | ዘውዱ | ደስታ | » » |
| 222 | ዘውዱ | ረዴ | መምሬ |
| 223 | ዘውዱ | ወ/ ጻድቅ | አቶ |
| 224 | ዘውዱ | ቸርነት | » » |
| 225 | ይርዳው | መሊዮን | » » |
| 226 | የሺጥላ | በነበሩ | ,, ,, |
| 227 | የሸዋሉል | መዝለቂያ | ,, ,, |
| 228 | የማነ ብርሃን | አበበ | ,, ,, |
| 229 | ይልሙ | ወንድሙ | ,, ,, |
| 230 | ይስሐቅ | ወ/ ዮሐንስ | የመቶ አለቃ |
| 231 | የሺ | መኰሪያ | አቶ |
| 232 | ይገዙ | ተክለ ሃይማኖት | ,, ,, |
| 233 | ይልማ | ደምሴ | ,, ,, |
| 234 | ዮሐንስ | ህሉተ ወርቅ | ,, ,, |
| 235 | ዮሐንስ | ደስታ | ,, ,, |
| 236 | ደምሴ | ዳምጤ | ሻምበል |
| 237 | ደምሴ | ኃ ማርያም | ሰርገ ማዦር |
| 238 | ደምሴ | ሀ ሚካኤል | ፊታውራሪ |
| 239 | ጆማ | ሮቢ | አቶ |
| 240 | ደጀኔ | ውድነህ | |
| 241 | ጃንከ | ጉደታ | |
| 242 | ደጀኔ | መታፈሪያ | |
| 243 | ደሳለኝ | ወርቁ | |
| 244 | ደምሴ | ደስታ | |
| 245 | ደበበ | ጨቢሳ | |
| 246 | ደበበ | ገብረ ሕይወት | |

| ተ ቍ | ስምና ያባት ስም ። | | ማዕረግ |
|---|---|---|---|
| 247 | ደጀኔ | ተሰማ | አቶ |
| 248 | ደሳለኝ | መንግሥቱ | |
| 249 | ደጉ | ወልደ ጊዮርጊስ | |
| 250 | ደበበ | ኀይሌ | |
| 251 | ዥሬር | ባስሚዲያን | |
| 252 | ግዛው | እንደሻው | |
| 253 | ገብረየስ | በለጠ | ሻለቃ |
| 254 | ገሠሠ | ነበና | » |
| 255 | ግዛው | ቱሉ | መቶ አለቃ |
| 256 | ጌታሁን | ተፈራ | አቶ |
| 257 | ገሥግሥ | ወልደየስ ። | |
| 258 | ጌታቸው | መሐሪ ። | |
| 259 | ጋሜ | አማኑች ። | |
| 260 | ገብሩ | ደሬሳ | |
| 261 | ገ/ ክርስቶስ | ሥዩም ። | |
| 262 | ገዛኸኝ | ሁነኛው ። | |
| 263 | ገብረ ሕይወት | ወንድሙ ። | |
| 264 | ጌታቸው | ወ አገኘሁ ። | |
| 265 | ገዛኸኝ | በዳሳ ። | |
| 266 | ገ/ ማርያም | ወየሳ ። | |
| 267 | ጌታቸው | ጓዴ ። | |
| 268 | ጌታቸው | ቢሻው ። | |
| 269 | ጌታቸው | አበበ ። | የመ/ አ ፡ |
| 270 | ጌታቸው | ነዋይ ። | አቶ |
| 271 | ጌታቸው | ወ/ ጊዮርጊስ ። | |
| 272 | ግርማ | ወ/ ጻድቅ ። | |
| 273 | ገሠሠ | ዘለቀ ። | |
| 274 | ጌታቸው | አስፋው ። | |
| 275 | ገዛኸኝ | ሞላ ። | |
| 276 | ግዛው | እንደሻው ። | |
| 277 | ጥግነህ | ወ/ አማኑኤል ። | ሻምበል ፡ |
| 278 | ጥላሁን | ወ/ ብርሃን ። | አቶ |

| ተ ቍ | ስምና ያባት ስም ። | | ማዕረግ |
|---|---|---|---|
| 279 | ጥጉ | ወ| ጻድቅ ። | |
| 280 | ጥላሁን | ዘለቀ ። | |
| 281 | ጥላሁን | ቢተው ። | |
| 282 | ጥበበ | ሀ ሥላሴ ። | |
| 283 | ጥላሁን | ተክሌ ። | |
| 284 | ጥላዬ | ካሣዬ ። | |
| 285 | ጥበበ | ሀ| ዮሐንስ ። | |
| 286 | ጥላሁን | ውቤ ። | |
| 287 | ጥላሁን | ወ ማርያም ። | |
| 288 | ጥላሁን | በዳኔ ። | |
| 289 | ጥላሁን | ንጋቱ ። | ሌ| ኰሎኔል ፡ |
| 290 | ጆጌ | ገዝሙ ። | |
| 291 | ፀጋዬ | ወንድም አገኘሁ ። | |
| 292 | ጳውሎስ | ገ| ኢየሱስ ። | |

## ማውጫ ።


፩ኛ ስለ መድኀኔ ዓለም ትምህርት ቤት አቋቋም ፩ኛ ክፍል ገጽ ፩ኛ

፪ኛ የልዑል መኰንን መስፍነ ሐረር አጭር ታሪክና የኢትዮጵያ የጦር ቦይስካውት ትምህርት ቤት ፪ኛ ክፍል ገጽ ፲ኛ

፫ኛ ልዑልነታቸው በትምህርት ቤቱ ይፈጽሙት የነበረው መልካም አገልግሎት ፫ኛ ክፍል ገጽ ፲፯ኛ

፬ኛ የዛሬው የስዊድን ንጉሥ ኢትዮጵያ መጥተው በነበረ ጊዜ ፬ኛ ክፍል ገጽ ፲፰ኛ

፭ኛ ተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንንበስደት አገር ፭ኛ ክፍል ገጽ ፳፫ኛ

፮ኛ ተወዳጁ መስፍን ልዑል መኰንን ከለንደን ወደ ካርቱም ከሱካን ወደ እናት አገራቸው ኢትዮጵያ ። ፮ኛ ክፍል ገጽ ፳፮ኛ

፯ኛ ስለ ዘመን አለዋወጥ ፯ኛ ክፍል ገጽ ፳፯ኛ

፰ኛ የልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ መስፍነ ሐረር ዜና ዕረፍት ፰ኛ ክፍል ገጽ ፳፰ኛ

፱ኛ የመጨረሻ መሰናበቻ ፱ኛ ክፍል „ „

፲ኛ ስለመልካም ሰው ትውልድ ፲ኛ ክፍል ገጽ ፴፫ኛ

፲፩ኛ የማይረሳ ታላቅ ውለታ ፲፩ኛ » » ፴፭ኛ

፲፪ኛ የቦይስካውቶች ማህበራዊ ድርጅት ፲፪ኛ » » ፴፮ኛ